# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን

## ማወቅና በአግባቡ መጠቀም

መለሰ ወጉ

**የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም**

*“Yëmënfës Kidus Sitotawochin mawëkina Bëa`gibabu Mëtëkëm”*

“Gifts of the Holy Spirit: Identification and proper application”

የመጀመሪያ እትም፤ መስከረም ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
First Edition, September 2000

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ነው።

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ፥ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለማባዛት፥ በቅድሚያ ከኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ዋና ጽሕፈት ቤት የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright © 2000 by Ethiopian Outreach Ministry
All rights reserved. No part of this book may be reproduced in any manner without written permission from Ethiopian Outreach Ministry except in the case of brief quotations in critical articles and reviews.

Produced by:

Ethiopian Outreach Ministry
P.O.Box 2241
York, PA 17405
United States of America

http://www.ethiopianoutreach.com

Ethiopia Office Address:
P.O.Box 7888, Addis Ababa, Ethiopia.

Printed in the United States of America

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ለይተን እንወቅ

<u>ምዕራፍ</u>

1. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ማወቅ፥ በአገልግሎታችን ፍሬያማ ያደርገናል............................ 14
2. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለአማኞች ሁሉ የሚሰጥ ነው............................................................ 31
3. መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ሥራ........................................................ 48
4. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን እንዴት ማወቅና መቀበል እንችላለን?.............................................. 61

## ክፍል ሁለት

## በንግግር የሚገለጡ ስጦታዎች

5. በጥበብ የመናገር ስጦታ..............................................80
6. በዕውቀት የመናገር ስጦታ............................................ 95
7. በልዩ ዓይነት ልሳን የመናገርና በልሳኖች የተነገረውንየመተርጎም ስጦታ.......................................108
8. ትንቢት የመናገር ስጦታ..............................................136
9. የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ..............................................159
10. የማስተማር ስጦታ.................................................... 170
11. የመምከር ስጦታ.......................................................182

12. የሐዋርያነት ስጦታ........................................................... 197
13. የእረኛነት ስጦታ..........................................................207

## ክፍል ሦስት

## በአገልግሎት የሚገለጡ ስጦታዎች

14. ሌሎችን የማገልገል ስጦታ........................................233
15. የመለገስ ስጦታ ....................................................252
16. የማስተዳደር ስጦታ ..............................................266
17. ምሕረት የማድረግ ስጦታ.........................................284

## ክፍል አራት

## በኃይልና በተአምር
## የሚገለጡ ስጦታዎች

18. የመፈወስ ስጦታ....................................................297
19. ተአምር የመሥራት ስጦታ.........................................315
20. የእምነት ስጦታ.....................................................328
21. መናፍስትን የመለየት ስጦታ.......................................347
22. በስጦታችን እንጠቀም - (ማጠቃለያ አሳብ)..............369

# መግቢያ

ያለንበት ዘመን፥ መንፈስ ቅዱስ በኃይልና በሙላት የሚንቀሳቀስበት የመጨረሻው ዘመን ነው። መንፈስ ቅዱስ ሰው ሠራሽ የሆነ ክልል ሳያግደው፥ በአንድ "ቤተ እምነት" (*denomination*) ውስጥ ብቻ ሳይወሰን፥ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በታላቅ ኃይል ሲሠራ በግልጽ የሚታይበት፥ አማኞች ከምንጊዜውም የበለጠ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን በሕይወታቸው የሚናፍቁበት ዘመን ነው። እግዚአብሔር አማኞችን በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላው፥ አሸናፊ የሆነ የክርስትና ሕይወት መኖር የሚችሉበትን ኃይል ለመስጠት፥ ለአገልግሎት ለማዘጋጀት፥ አማኞችን ሁሉ በዓላማ አንድ ለማድረግ፥ እግዚአብሔር አብን ለማክበርና እንዲሁም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ነው።

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመረምር፥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በነበረበት ዘመንና አካባቢ፥ የሰይጣንም እንቅስቃሴ በዚያው መጠን ብርቱ እንደነበረ እንገነዘባለን። መንፈስ ቅዱስ ሲንቀሳቀስ፥ ሰይጣን ብዙ ምርኮኞቹን ስለሚያጣ፥ ትልቅ ተጋድሎ ያደርጋል። በተቻለው መጠን የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴ የሚገታበትንና ሂደቱን ወደ ኋላ የሚጎትትበትን ዘዴዎች ይሸርባል። ከዘዴዎቹ መካከል አንደኛው፥ መንፈስ ቅዱስን የሚመስል፥ የራሱን የውሸት (counterfeit) እንቅስቃሴ መፍጠርና ብዙዎቹን ከመስመር ማስወጣት ነው። ሁለተኛ፥ ከትምህርት ማጣት የተነሳ አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚፈጽሙትን ጥቃቅን ስህተቶች እያጎላ በማሳየት፥ ክርስቲያኖች "የመንፈስ ቅዱስን" እንቅስቃሴ እንዲጠራጠሩ፥ እንዲጠሉና ችላ እንዲሉ በማድረግ ነው።

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ፥ ከላይ የገለጽናቸውን የሰይጣንን ተንኮሎችና ዘዴዎች ለማጋለጥ ነው። የምናጋልጠውም፥ አንደኛ፥ አማኞች ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ እውነቱንና ትክክለኛውን እንዲያውቁና ስጦታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት በማድረግ፥ ሁለተኛ፥ በቂ ትምህርት ባለማግኘት ምክንያት አንዳንድ ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ያለአግባብ በመጠቀም ስላበላሹ ብቻ፥ ስጦታውን ንቆ ችላ ማለት ትክክል እንዳልሆነ በማስተማር ነው። ይህ መጽሐፍ፥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ፥ ዘመን ያለፈበት፥ በእኛ ጊዜ የማይሠራ፥ ወይንም በአንድ አነስተኛ *"ቤተ እምነት"* (denomination) ውስጥ ያሉ የሃይማኖት ወግ አጥባቂዎች ብቻ የሚከተሉት የሃይማኖት ልምምድ እንዳልሆነ ይገልጻል። ይህ መጽሐፍ፥ "የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴን የሚያምኑና በሕይወታቸው የሚለማመዱ፥ በአዕምሮ ያልበሰሉ ሰዎች ብቻ ናቸው" በማለት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታንና እንቅስቃሴውን ችላ እንድንል የሚያደርገንን የሰይጣንን የማሳሳት ዘዴ ይገልጣል ብለን እናምናለን።

"በመንፈስ ቅዱስ" ስም ብዙ አዳዲስና እንግዳ ትምህርቶች በበዙበት በአሁኑ ዘመን፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ትክክለኛና *"መጽሐፍ ቅዱሳዊ"* ትምህርት መስጠት፥ ከምንጊዜውም የበለጠ አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምዕመናኖቻቸውን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማስተማር፥ ስጦታቸውንም በትክክል አውቀው እንዲያገለግሉ የአገልግሎት ዕድል መስጠት አለባቸው። ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ለምዕመናን ብቻ ሳይሆን፥ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ጭምር ነው። ይህ መጽሐፍ በሁሉም *"ቤተ እምነቶች"* ውስጥ ላሉት አማኞች እንዲሆን እንጂ፥ አንድ *"ቤተ እምነት"* ውስጥ ላሉት አማኞች ብቻ ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም። ከመጠን በላይ ከባድ ሆኖ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አዲስ የሆኑት ግራ



እንዳይጋቡበት፥ በጣምም ዝቅ በማለቱ በእምነታቸውና በአዕምሮ ችሎታቸው የላቁ አማኞች ተራ ነው ብለው እንዳይጥሉት፥ መካከለኛውን ደረጃ ይዞ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው።

ቀደም ሲል አዘጋጅቼ ያወጣኋቸውን መጽሐፍት፥ ዛሬ ሳነባቸው፥ አንዳቸውም እኔ እንዲሆኑ ከምፈልጋቸው ደረጃ የደረሱ መስለው አይታዩኝም። የገንዘብና የጊዜ አቅሜ ፈቅዶልኝ፥ ለሁለተኛ እትም አዘጋጅቼ ባቀርብ፥ የተሻለና ያማረ አድርጌ እንደማቀርብ አልጠራጠርም። በአሁኑ ጊዜ አዘጋጅቼ ያቀረብኩትን፥ ይህን *"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም"* የሚለውን መጽሐፌን ከአሥር ዓመት በኋላ ብጽፈው፥ ከዚህ የተሻለ አድርጌ እንደማወጣው እርግጠኛ ነኝ። ይህን ያልኩበት ምክንያት፥ በአስር ዓመት ውስጥ በአስተሳሰብ፥ በአጻጻፍ ስልት፥ በአዕምሮ ብስለት፥ የሚኖረኝ "የሥነ መለኮት" ዕውቀት፥ ዛሬ ካለኝ በጣም የበለጠና የተሻለ እንደሚሆን ስለማምን ብቻ ነው። በተጨማሪም፥ መጽሐፉ "ፍጹም እንከን የሌለበት፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን በሚመለከት አሳብ ላይ ለሚነሳው ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ፥ ፍጹም አጥጋቢ የሆነ መልስ መስጠት ይችላል" በማለት እንዳልሆነ ለመግለጽ ነው። እስከበስል፥ የተሻለ ጽሁፍ ማቅረብ እስከምችል ድረስ ሌላ አሥር ዓመት ልጠብቅ ብል፥ በየቦታው በመንፈስ ቅዱስ ስም፥ ቁጥር ስፍር የሌላቸው "እውነት መሳይ ትምህርቶች" እየተፈጠሩ፥ እውነትን የተጠሙ ክርስቲያኖችን የበለጠ ያወናብዳሉ ብዬ ስለፈራሁ፥ በወቅቱ አቅሜና ችሎታዬ የፈቀደልኝን ለማቅረብ ወሰንኩ።

አዘጋጅቼ ካወጣኋቸው መጽሐፍት ውስጥ፥ ረጅም ጊዜ የወሰደብኝ፥ ይህ *"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም"* የሚለው መጽሐፍ ነው። አርዕስቱ ከባድ፥ አከራካሪ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ፥ የተለያየ የእምነት አቋም ያላቸ

ውን ሰዎች ሁሉ ለማገልገል ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ የሥነ መለኮት ዕውቀት ያላቸው፥ በአገልግሎት የቆዩ፥ ጌታ በልዩ ልዩ መንገድ የተጠቀመባቸው ብዙ ወንድሞችና እህቶች መጽሐፉ ለሕትመት ከመቅረቡ በፊት ጊዜ ወስደው በጥንቃቄ አንብበው አስተያየት እንዲሰጡበት ስለፈለግሁ ነው። የነዚህን ወንድሞችና እህቶች አስተያየት የፈለግሁበት ምክንያት፥ “ብራቮ መለሰ! ጥሩ መጽሐፍ ጽፈሃል” እንዲሉኝ፥ አንባቢዎቼን “ጥሩ መጽሐፍ ነውና አንብቡት” በማለት እንዲያባብሉልኝ አይደለም። ነገር ግን እኔ ያላየሁትን የመጽሐፉን ጉድፍ እንዲያዩልኝ፥ አንባቢውን የሚገፋተር ኃይለ ቃል፥ ወይንም ከባድ ቋንቋ ተጠቅሜ እንደሆን፥ በመግለጽ ፈንታ የበለጠ ያደ ናግር እንደሆን አይተው እንዲጠቁሙኝ ነው። መጽሐፉን አንብበው አስተያየት እንዲሰጡኝ ከጠየቅኋቸው ወንድሞችና እህቶች ከጠበቅሁት በላይ ከእያንዳንዳቸው ጠቃሚ አሳቦችን አግኝቻለሁ። “ይለወጥ፥...ይውጣ፥ ይቅር፥ ይጨመር፥ ይብራራ... ወዘተ” ያሉኝን በተቻለኝ መጠን ለማስተካከል ሞክሬአለሁ። ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው በጥንቃቄ፥ መስመር በመስመር ያነበቡት መሆኑን በሰጡኝ አስተያየቶች ተገንዝቤአለሁ። እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ ከማለት በስተቀር ሌላ የምላቸው የለም። ስማቸውን መጥቀስ አስፈላጊ ቢሆንም፥ ያለመጥቀሴን የመረጥኩበት ጥሩ ምክንያት አለኝ። ልቤን ደስ ሊያሰኙ፥ ውስጤን ሊያሞቁ የሚችሉ ብዙ የምስጋና ቃላት ገልጸውልኛል። የተጻፈልኝን ምስጋናውን ትቼ፥ እንዳስተካክል ከተጻፉልኝ ብዙ አስተያየቶች መካከል፥ ጥቂቶቹን ለምሳሌ ያህል ልጥቀስላችሁ፥

- *“ጸሐፊው ያለው ጠንከር ያለ ስሜት አንዳንድ ቦታ በጣም ኃይለ ቃል ስላለው መጽሐፉ በቁጣ የተጻፈ ይመስላል። ይህን መጽሐፍ ለረዥም ዓመታት የተለያየ ትውልድ ሲያነበው ሊፈጥር የሚችለው ነገር ምን ይሆን? ያሰኛል።”*



- *“በአገልግሎት ዘመንህ ካየሃቸው በጸጋ ስጦታዎች ስም ከተደረጉ ስሕተቶች ምሳሌዎችን ሰጥተሃል፤ ሆኖም በረዥም የአገልግሎት ዘመንህ ካጋጠሙህ ውስጥ ብዙ ምሳሌዎችን ብትጨምር ለዚህ ትውልድ ትልቅ ትምህርት ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ። እባክህን ብዙ ምሳሌዎችን ስጠን።”*
- "Denominations *የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በአሁኑ ጊዜ መላ ወንጌላውያን፥ የቤተ ክርስቲያናት ምሁራን የሚጠቀሙበት ቃል “ቤተ እምነት” (በነጠላ ቁጥር) ወይም “ቤተ እምነቶች (በብዙ ቁጥር) የሚለውን ሐረግ ስለሆነ ይህንን ብትጠቀም መልካም ነው።”*
- *“በመጽሐፉ ገጽ ... ላይ የሚገኘው ዐረፍተ ነገር “የመንፈስ ፍሬ የማይታይበት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ዓየር የሌለበት የመኪና ጎማ ማለት ነው” ይላል። ይህ ዓይነት አባባል በእኔ ግምት የመጽሐፉን ቁንጅና የሚቀንስ መስሎ ታይቶኛል።”*
- *“ ‘...የሐዋርያው ጳውሎስ ደብዳቤ’ የሚሉ ቃላት አሉ። ነገሩ እውነት ቢሆንም ደብዳቤ የሚለው ቃል ለበርካታ የአገራችን አንባቢዎች ነገሩን ያቃለልከው መስሎ ይሰማቸዋል። ስለዚህ ደብዳቤ የሚለው ቃል “መልዕክት” በሚለው ቢተካ ይሻላል።”*
- *“...በገጽ ... ላይ የሐዋርያት ሥራ ሽማግሌዎች ሲል የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ማለቱ እንደሆነ የተረዳነው አይመስለኝም ይላል። ይህን ለማለት የሚያስደፍር ማስረጃ እናገኛለን ወይ? ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የሙሉ ጊዜና የትርፍ ጊዜ አገልጋይ ብሎ በመከፋፈል ያሳየናል ወይ? የጌታ ልጅ የሆነ ሁሉ በየተሠማራበት መስክ በቃሉና በሥራው ትክክለኛ የጌታ ምስክር ከሆነ እርሱም በተሰጠው ጊዜ ሁሉ አገልጋይ ነው። ስለዚህ በስብከት በማስተማር በመምከር ወዘተ... የሚውለው የሙሉ ጊዜ፥ በሌላ ሥራ ተሠማርቶ ጌታን በተግባሩ ሲመሰክር የሚውለው የትርፍ ጊዜ አገልጋይ ነው ማለት የሚቻል አይመስለኝም።... በዚህ ነገር ላይ አንድ አስታራቂ ሃሳብ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቢጠቆም መልካም ይመስለኛል።”*

- *“ገጽ ... ላይ ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች በስሜት ብቻ ሲሰክሩ የሚታዩት“ የሚለውን በተሻለና ሚዛናዊ በሆነ ቃል ወይም አገላለጽ ቢተካ።”*
- *“ከገጽ .... ድረስ የተገለጸው የሐዋርያነት ስጦታ ጉዳይ ዛሬ በአገራችን አከራካሪና አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። በአሁኑ ጊዜ ስለ (Apostolic Ministry) አዲስ ትምህርት የተጀመረ ስለሆነ አንዳንድ አገልጋዮች በሹመት ሐዋርያ እየተደረጉ ነው። ይህን ወቅታዊ ችግር ብትገልጸው ጠቃሚ ይሆናል። ጽሑፉ አሁን ባለ መልኩ በመነሳት ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ አይሰጥም።”*
- *“የመጽሐፉን ሐሳብ ጠቅለል ባለ መልክ ይዘት ያለው መደምደሚያ አንቀጽ ቢኖረው ጥሩ ይሆናል።”*

በሰጡኝ አስተያየትና ምክር መሠረት የምችለውን ሁሉ አስተካክዬና ለውጬ በማቅረቤ፥ የመጽሐፉ ይዘትና መልክ የበለጠ እንደተሻሻለ ለመግለጽ እወዳለሁ። ይሁን እንጂ፥ አሁንም ገና ብዙ እንደሚቀረው አምናለሁ። በተለያየ “ቤተ እምነት” ውስጥ ያሉትን ሁሉ ያረካል፥ አንባቢዎቼ ሁሉ ከእኔ አሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ ትስማማላችሁ ብዬ ፈጽሞ አላምንም። በሁሉም ባንስማማ፥ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ እንስማማ ይሆናልና፥ በአጠቃላይ “መጽሐፉ አይረባም” ብላችሁ ከምትጥሉት፥ የሚስማማችሁን ወስዳችሁ፥ የማይስማማችሁን እንድታልፉት መምከር እፈልጋለሁ። በአሁኑ ዘመን በዚህ አርዕስት መጽሐፍ አዘጋጅቶ ማቅረብም ሆነ ትምህርት መስጠት ከባድ እንደሆነ እገነዘባለሁ። “ከሥርዓት አንውጣ፥ ስጦታችንን በአግባቡ እንጠቀም” ብሎ መምከርና ማስተማር “የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ” እንደሚያሰኝ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ፥ እውነቱን ማስተማር ኃላፊነት እንዳለብኝ፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ ተጠያቂ እንደሚያደርገኝ ስለማምን፥ በዚህ ከባድ አርዕስት የማውቀውን፥ የተለማመድኩትን፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያስተማረኝን፥ ለአሁኑና ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ ጥቅም እንዲሆን፥ ይህንን ትምህርት አቅርቤአለሁ።



የእምነቴን አቋም ለምትጠራጠሩ፥ ይሄ መጽሐፍ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያለሁበትን የእምነት አቋም በበቂ ሁኔታ ካልገለጸላችሁ፥ *“የእምነት አንቀጼ”* ይኸውላችሁ፥

- በመንፈስ ቅዱስ ሙላት አምናለሁ።
- መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፉት ስጦታዎች ሁሉ አምናለሁ።
- ስጦታዎቹ እንደ ጥንቱ በእኛም ዘመን ይሠራሉ ብዬ አምናለሁ።
- እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አለው ብዬ አምናለሁ።
- ስጦታችንን በአግባቡና በስነ ሥርዓት መጠቀም እንዳለብን አምናለሁ።
- ስጦታችን እግዚአብሔርን ለማክበር እንጂ ራሳችንን፥ ወይንም ሰውን ለማክበር እንዳልሆነ አምናለሁ።
- ዓለምን በወንጌል ለመድረስ እግዚአብሔር *“የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን”* መሣሪያ አድርጎ እንዳስነሳ በሙሉ ልቤ አምናለሁ።

ስለሆነም፥ “አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን” ምዕመናኖቿን ለአገልግሎት እንድታዘጋጅ ይረዳል ብዬ በማመን፥ ይህን *“የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም”* የሚለውን መጽሐፌን፥ በትህትና አበረክታለሁ። የሚያነቡት ሁሉ እንዲማሩበትና እንዲባረኩበት ምኞቴና ጸሎቴ ነው። ይህንን መጽሐፍ አዘጋጅቼ እንዳቀርብ በልዩ ልዩ መንገድ የረዱኝን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

መለሰ ወንድ

# ክፍል አንድ

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ለይተን እንወቅ

ምዕራፍ 1 —— 14
የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ማወቅ፥
በአገልግሎታችን ፍሬያማ ያደርገናል።

ምዕራፍ 2 —— 31
የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ
ለአማኞች ሁሉ የሚሰጥ ነው

ምዕራፍ 3 —— 48
መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት
ውስጥ የሚሠራው ሥራ

ምዕራፍ 4 —— 61
የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን
እንዴት ለይተን ማወቅ እንችላለን?

ምዕራፍ

1

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ማወቅ፣ በአገልግሎታችን ፍሬያማ ያደርገናል

ማንኛውም በክርስቶስ አምኖ የዳነ አማኝ፣ ሙሉ ጊዜውን ለወንጌል ሥራ የሰጠ ባይሆንም፣ *"በወንጌል ሥርጭት"* ውስጥ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው እናምናለን። ይሁን እንጂ፣ በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለውን ትክክለኛ ስፍራ ካላወቀ፣ ወይንም ምን ዓይነት የአገልግሎት ድርሻ እንዳለው በደንብ ካልተረዳ፣ የወንጌሉን ስርጭት በማፋጠን ፈንታ ይበልጥ ወደ ኋላ እንደሚጎትተው ግልጽ ነው። እዚህ ላይ ችግሩ ሁለት ዓይነት ነው። ይኸውም፣

1ኛ) *"አማኝ ሁሉ አገልጋይ"* ከሆነ፣ "ማገልገል አለብኝ" በማለት ብቻ ያለስጦታውና ያለቦታው አገልግሎት ውስጥ ይገባና ራሱንም ሆነ ሌላውን ሲጎዳ ይገኛል። ማንኛውም አማኝ ያለስጦታውና ያለቦታው ገብቶ ሲያገለግል፣ ብዙ ጊዜ ከሌሎች አገልጋዮችና እንዲሁም ከሚያገለግለው ሕዝብ ጋር መጋጨቱ ብቻ ሳይሆን፣ በአገልግሎቱም ፍሬያማ

ያፈራ መሆኑ ነው። ግጭቱ ተደጋጋሚ ሲሆንበት፣ ተስፋ ቆርጦ ከአገልግሎቱ ይወጣል፤ ወይንም የከፋ እንደሆነም ከነ ጭራሹ ከጌታ ሊርቅ ይችላል።

2ኛ) *"ስጦታዬ ነው"* በሚለው "የአገልግሎት ዘርፍ" ውስጥ ገብቶ ለማገልገል ዕድል ሳያገኝ የቀረ እንደሆነ ደግሞ፣ ያ አማኝ ያለው ስጦታ በተግባር ላይ ባለመዋሉ ምክንያት "ቤተ ክርስቲያን" ትጎዳለች። እንዲሁም አማኙ "የአገል ግሎት በር አልተከፈተልኝም" በማለት በቅሬታ ስሜት ውስጥ ስለሚኖር፣ ደስታ የሸሸው ክርስቲያን ይሆናል።

## 1. "የአገልግሎት ጥሪ" እና "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ" ያላቸው ልዩነት

ብዙዎቻችን *"በአገልግሎት ጥሪና"* እንዲሁም *"በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ"* መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ አናውቅም። አንዳንድ አማኞች "*ሥራዬን ትቼ ወንጌላዊ ወይንም መጋቢ ሆኜ እንዳገለግለው ጌታ ጠርቶኛል*" ሲሉ እንሰማለን። ይሁን እንጂ፣ "ጥሪ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ብዙዎቹ የተረዱት አይመስለንም። እግዚአብሔር ለልዩ ዓላማ የተለያዩ ሰዎችን በእኛ ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ በጥንት ዘመንም ይጠራ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። በሐዋርያት ዘመን እግዚአ ብሔር የተለያዩ ሰዎችን ለተለያየ አገልግሎት ይጠራ ነበር። *"እነርሱ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩና ሲጾሙ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ አለ"* (የሐዋ. 13፥2)።

*"ጥሪ"* ስንል ምን ማለታችን ይሆን? "ጥሪ" ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ጋር እንዴት ይለያል? ወይንም ግንኙነታቸው እንዴት



ነው? እግዚአብሔር ወንጌል ላልደረሳቸው ሕዝቦች ወንጌልን እንድናዳርስ በአንዳንዶቻችን ልብ ውስጥ ልዩ የሆነ ሸክም እንዲሰማን ያደርጋል። ያ ሸክም ሌላ ነገር ሳይሆን ከእግዚአብሔር የመጣ የአገልግሎት *"ጥሪ"* ነው። ወንጌልን እንድናሰራጭ እግዚ አብሔር ሲጠራን፣ ወንጌላዊ መሆን የሚያስችለንን የመንፈስ ቅዱስ *"ስጦታ"* ሳይሰጠን እንዲሁ ባዶ እጃችንን እንደማይልከን የታወቀ ነው። *"አገልግሎታችንን መፈጸም"* የሚያስችለንን ስጦታ በመስጠት ለአገልግሎቱ ዝግጁ ያደርገናል። የምናገለግልበትን ስጦታ ከሰጠን ደግሞ፣ የአገልግሎት በር ከፍቶ የት ሄደን ማገልገል እንደምንችል፣ እንዲሁም በምን ዓይነት ሁኔታ ማገ ልገል እንዳለብን በመግለጽ "ጥሪውን" ይሰጠናል። በዚህ ዓይ ነት ሁለቱም የተያያዙ እንደሆኑ እናያለን። አንዳንድ አማኞች "እግዚአብሔር የመስበክን ስጦታ እንደሰጠኝ አምናለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዳልሰብክ መድረኩን ስለ ከለከሉኝ፤ በስብከት ማገልገል አልቻልኩም" ብለው ሲያማርሩ ይሰማሉ። ሌሎች ደግሞ "የመስበክ ዕድል ብዙ ያጋጥመኛል፤ እኔ ግን መድረክ ላይ ቆሜ መስበክ ያስፈራኛል፤ ችሎታዬንም እጠራጠረዋለሁ" የሚሉ አሉ። በመሠረቱ ለመስበክ የሚያስች ለውን ስጦታ ሳይሰጥ፣ እግዚአብሔር ማንንም "ሰባኪ ሁን" ብሎ አይጠራም። የሰባኪነት ስጦታ ሰጥቶ ደግሞ የሚሰብክበትን ሥፍራ አይዘጋበትም። እግዚአብሔር ወንጌላዊ መሆን የሚያስ ችለንን ስጦታ እንደሰጠን ብናውቅም፣ የሰጠንን ስጦታ የት አገር፣ ወይንም የት ቤተ ክርስቲያን ሄደን መጠቀም እንዳለ ብን ላናውቅ እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ አገልግሎታችንን የምንፈጽምበት ጊዜውና ሰዓቱ ሲደርስ፣ ልዩ የሆነ ምሪትን በመስጠት፣ ወይንም ሌሎችን በሮች ሁሉ ዘግቶ፣ አንዱን ብቻ በመክፈት ፈቃዱን እንድናውቅ የሚያደርግበት ጊዜ አለ። ጳውሎስና ሲላስ አንድ ጊዜ ለአገልግሎት ወደ ቢትኒያ ለመሄድ አስበው ነበር፤ *"ነገር ግን የኢየሱስ መንፈስ ወደዚያ እንዲሄዱ*

*አልፈቀደላቸውም"* ነበር (የሐዋ. 16፥7)። የቢታንያ በር በዚያን ጊዜ ዝግ ነበር። ይሁን እንጂ፥ የመቄዶንያ በር ክፍት ነበር። *"አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ ወደ መቄዶንያ ተሻገርና ዕርዳን! እያለ ሲለምነው ጳውሎስ በራእይ አየ"* (የሐዋ. 16፥9)። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ለጳውሎስ የአገልግሎት ጥሪ ሲያደርግለት እናያለን። እኛም በዚህ ዓይነት ግልጽ የሆነ የአገልግሎት ጥሪ እንዲደርሰን የምንፈልግበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ፥ እግዚአብሔር አማኞችን ወደ አገልግሎት የሚጠራበት የተለያየ መንገድ እንዳለው መዘንጋት የለብንም።

ቁጥራቸው እጅግ በጣም ጥቂት የሆኑትን ብቻ ሥራቸውን ትተው በሙሉ ጊዜ አገልጋይ እንዲሆኑ ጥሪ ያደርግላቸዋል እንጂ፥ እግዚአብሔር አማኞችን ሁሉ ሥራቸውን እየተው በመውጣት እንዲያገለግሉ አይጠራም። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር መንግሥት ግንባታ ውስጥ አማኞች ሁሉ ተሳትፎ ወይንም ድርሻ የላቸውም ማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ለማስፋፋት እንድንችል፥ መንፈስ ቅዱስ ምን ዓይነት ስጦታ እንደሰጠን አለማወቃችን፥ በአገልግሎታችን ፍሬያማ እንዳንሆን ያደርገናል። ለዚህ ነው ጳውሎስ *"ወንድሞቼ ሆይ! አሁን ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እውነተኛውን ነገር እንድታውቁ እፈልጋለሁ"* (1 ቆሮ. 12፥1) ያለው። ጳውሎስ *"እንድታውቁ እፈልጋለሁ"* ሲል፥

1ኛ) የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ስጦታዎች የትኞቹ እንደሆኑ "እንድታውቁ" ማለቱ ሲሆን፥

2ኛ፥ በአገልግሎታችን ፍሬያማ እንድንሆን የሚያስችለን ለእያንዳንዳችን በግል የተሰጠን ስጦታ ምን እንደሆነ ለይተን "እንድናውቅ" ማለቱ ነው።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው ችግር፥ ከምክንያቶቹ መካከል አንደኛው፥ አማኞቹ ስጦታቸውን ለይተው



ካለማወቃቸው የተነሳ የመጣ ነበር። ለዚህ ነው ጳውሎስ *"ወንድሞች ሆይ! አሁን ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እውነተኛውን ነገር እንድታውቁ እፈልጋለሁ"* ያላቸው። ይህን ዓይነቱ ችግር በእኛም ዘመን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ጎልቶ ይታያል። አንዳንድ አማኞች ያለስጦታቸውና ያለቦታቸው ለማገልገል ሲሞክሩ፥ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ብዙ ግጭትና አለመስማማት ሲፈጠር በግልጽ ይታያል።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ የተለያየ አስተያየትና እምነት ያላቸው፥ በእኛ ዘመን ያሉት አማኞች ብቻ ሳይሆኑ፥ በየዘመናቱ የነበሩ መንፈሳዊ አባቶችም የተለያየ እምነት እንደነበራቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል።

- ☐ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች "በሐዋርያት ዘመን ብቻ እንጂ በእኛ ዘመን አይሠራም" በማለት የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ችላ የሚሉ ክፍሎች አሉ።
- ☐ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ብቻ ሳይሆን፥ በእኛም ዘመን ይሠራል" ብለው የሚያምኑ ክፍሎችም አሉ። "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ማወቅ" ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆን የተረዱ፥ እንዲሁም "ስጦታዎቹ በእኛም ዘመን ይሠራሉ" ብለው ያመኑና የተቀበሉ አንዳንድ የአሜሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት፥ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉትን የቤተ ክርስቲያናቸው አባል አድርገው ከመቀበላቸው በፊት፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ካስተማሩ በኋላ እያንዳንዱ አማኝ የተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምን እንደሆን እንዲያውቅ ያደርጉታል። ስጦታውን ካላወቀ ግን የቤተ ክርስቲያናቸው አባል አድርገው አይቀበሉትም። ይህን የሚያደርጉበት ዋናው ምክንያት አማኞች ስጦታቸውን ካላወቁ፥ ፍሬያማ ሊያደርጋቸው በሚችለው አገልግሎት ውስጥ ገብተው እንዳይሳተፉ የሚያ

ደርጋቸው ከመሆኑም በላይ፥ ያለስጦታቸውና ያለቦታቸው ለማገልገል በመሰለፋቸው ምክንያት ብዙ ግጭትና አለመግባባት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉI እንዲሁም በአገልግሎታቸው የጠበቁትን ዓይነት ፍሬ ማየት ባለመቻላቸው ምክንያት ተስፋ ቆርጠው ራሳቸውን ከአገልግሎት ያስወጡ ይሆናል ብለው ስለሚያምኑ ብቻ ነው።

- ❑ ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተለያየ አስተያየትና እምነት ውስጥ አልፋለች። የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አባቶችም የራሳቸው የሆነ የተለያየ አስተያየት ነበራቸው፥
- ❑ እነ *ጁስቲን ማርትየር*፥ *ኢራንየስ*፥ ተአምራዊ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን አሁንም ይሠራሉ ብለው ሲያምኑ፥
- ❑ *ተርቱልያንም* ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተቃውሞ አልነበረውም።
- ❑ በአራተኛው ክፍለ ዘመን ታዋቂ የነበረው *ቢሾፕ ሂላሪ* የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለማመድን ይደግፍ ነበር።
- ❑ በ5ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው *አጉስቲን* ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለሃዋርያት ዘመን ብቻ የተሰጠ ነው ብለው የሚያምኑትንም ሆነ እንዲሁም አሁንም በእኛ ዘመን ይሠራል የሚሉትንም፥ ሁለቱንም ይደግፍ ነበር ይላሉ።
- ❑ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው *ቶማስ አኪነስ*፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ከሃዋርያት በኋላ ይሠራሉ ወይንም አይሠሩም ብሎ በግልጽ ባያስተምርም፥ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን ግን ያስተምር ነበር።
- ❑ በተሀድሶ (ሪፎርሜሽን) ዘመን፥ እንቅስቃሴውን ይመሩት ከነበሩት፥ ስማቸው ጎልቶ ይጠራ የነበሩት *ማርቲን ሉተርና*



*ጆን ካልቪን* ነበሩ። እነዚህ ሁለት የተሀድሶ መሪዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ብዙ አላስተማሩም። *ሉተር* የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሃዋርያት ዘመን ብቻ የሆነ ልምምድ ነው ባይልም፥ በወቅቱ በራሱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲታይ አላደረገም። *ጆን ካልቪንም* ስጦታዎቹ በሃዋርያት ዘመን የተፈጸሙ ናቸው ይበል እንጂ፥ ከሐዋርያት በኋላም ይህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሥራቱን አልካደም። የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ በታሪክ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴና ሥራ ምን ያህል ተቀባይነት እንደነበረውና እንዳልነበረው ለማመሳከር ስላልሆነ፥ ታሪካዊ መግለጫዬን እዚሁ ላይ እቋጭና ወደሚቀጥለው ነጥብ አልፋለሁ።

ትኩረት ለመስጠት የምፈልገው አሁን እኛ ባለንበት ዘመን፥ በግል ሕይወታችን፥ በቤተ ክርስቲያናችን የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ምን ዓይነት ሥፍራ እንዳላቸው መመርመር ላይ ነው። ለመሆኑ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ማወቅ ያለባቸው እነማን ይሆኑ? ክርስቲያኖች ሁሉ፥ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ የሚያምኑና፥ እርሱን ከልባቸው መከተል የሚፈልጉ ሁሉ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማወቅ ይገባቸዋል። እኔና እናንተ ቤተ ክርስቲያናችን ጤናማ ሆና እንድታድግ፥ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለአካባቢያቸው የሚያንጸባርቁ አማኞች ያሉባት እንድትሆን ከፈለግን፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምን እንደሆነ ለማወቅ መሞከር ይገባናል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ በጣም ማወቅ እንደሚያስፈልጋቸው የተገነዘበው ጳውሎስ፥ *"...ስለ መንፈሳዊ ነገርም ወንድሞች ሆይ! ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ"* ይላቸዋል (1 ቆሮ. 12፥1)። ዛሬም እኛ ባለንበት ዘመን ስለ መንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴና ስጦታዎች ማወቅ የሚገባቸው ጥቂቶች ብቻ ሳይሆኑ በየትኛውም ሥፍራ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ናቸው።

## 2. መንፈሳዊ ስጦታችንን ካላወቅን፣ በስጦታችን መጠቀም አንችልም

በአገልግሎታችን ፍሬያማ መሆን የምንችለው፣ ስጦታችንን አውቀን፣ በስጦታችን ማገልገል ስንችል ብቻ ነው። ይህን ስንል በአገልግሎት ላይ የተሠማሩት ሁሉ ስጦታቸውን አውቀው፣ በስጦታቸው የሚያገለግሉ ናቸው ማለት አይደለም። ብዙ አማኞች ስጦታቸውን ሳያውቁ የሚያገለግሉ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ በአገልግሎታቸው የሚፈለገውን ያህል ፍሬያማ አልሆኑም።

የአሜሪካ ኢኮኖሚ ከመጠን በላይ ደካማ በነበረበት ዘመን፣ ቴክሳስ ውስጥ *ሚስተር ያትስ* የተባለ፣ በበግ ዕርባታ የሚተዳደር አንድ ሰው ነበር። በጎቹ ሳር የሚግጡበትን መሬት መጀመሪያ ሲገዛ ከባንክ ተበድሮ ስለነበረ፣ በየወሩ ወለዱንና ዋና ገንዘቡን ለመክፈል ከፍተኛ ውጥረት ነበረበት። አንዴ እንዲያውም መክፈል አቅቶት መሬቱን ባንክ ሊወስድበት ለትንሽ ነው ያመለጠው። በበግ እርባታው በሚያገኘው ገንዘብ ቤተሰቡን ለመመገብ፣ ልብስ ለማልበስ ባለመቻሉ ከመንግሥት መጠነኛ የሆነ ድጎማ ይደረግለት ነበር። አንዳንድ ቀን በጎቹን ሣር እንዲግጡ ካሰማራ በኋላ ከሜዳው ላይ ቁጭ ብሎ የምዕራብ ቴክሳስን ኮረብቶች እያየ፣ ለባንክ የሚሰጠውን የወሩን ክፍያ እንዴት አድርጎ ወይንም ከየት አምጥቶ መክፈል እንደሚችል በማሰብ ከመጠን በላይ የሚጨነቅበት ጊዜ ነበር።

አንድ ቀን ከአንድ ነዳጅ ማጣሪያ ኩባንያ የተላኩ የነዳጅ ማጣሪያ ባለሚሎች፣ መሬቱ ላይ ምናልባት ነዳጅ ሳይኖር እንደማይቀር ከገለጹለት በኋላ፣ ቆፍረው መመርመር ይችሉ እንደሆን ፈቃድ ጠየቁት። ከመቆፈራቸው በፊት ነዳጅ ከተገኘ ምን ያህል ገንዘብ ነዳጁን ባወጡ ቁጥር እንደሚከፍሉት ተነጋግረው የስምምነት ውል ተፈራረሙ። መጨረሻ ላይ አንድ



ሺ አንድ መቶ አሥራ አምስት ጫማ ከቆፈሩ በኋላ ብዙ የነዳጅ ክምችት አገኙ። በቀን 80 ሺ በርሜል ነዳጅ ያወጡ ጀመር። በየቀኑ 80 ሺ በርሜል እያወጡ፣ ከ30 ዓመት በኋላ በዚያ መሬት ላይ በቀን 125 ሺ በርሜል ማውጣት የሚችሉበት የነዳጅ ክምችት እንዳለ ታወቀ። ያ ሁሉ ሀብት *የሚስተር ያትስ* ነበር። ያንን መሬት በገዛበት ቀን በመሬቱ ላይ ያለውን ነዳጅ ዘይትም ሆነ ማንኛውንም ዓይነት ንጥረ ነገር የመውሰድና የመጠቀም ሙሉ መብት ነበረው። ይሁን እንጂ በመሬቱ ላይ ምን ያህል ከፍተኛ ሀብት እንደነበረ ባለማወቁ ለብዙ ዘመን በድህነት ተኮማትሮ ይኖር ነበር። ብዙ ሚሊዮን ብር ያለው ሀብታም መሆን ሲችል፣ ፍጹም ድሃ፣ በመንግሥት ዕርዳታ ብቻ የሚኖር ምስኪን ሰው ሆኖ ይኖር ነበር። ዋናው ምክንያት በመሬቱ ላይ ብዙ ብር ሊያስገኝለት የሚችል ነዳጅ መኖሩን ባለማወቁ ብቻ ነበር።

በዘመኑ ያለነው ክርስቲያኖችም፣ አብዛኛዎቻችን ተመሳሳይ ችግር አለብን። እግዚአብሔር የሰጠን ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፣ ምን እንደሆነ ባለማወቅ፣ ወይንም በእርሱ ፈቃድ ሥር በመኖራችን ምክንያት ምን መሆን እንደምንችል ባለመገንዘብ፣ በመንፈሳዊ ድህነትና ድካም ውስጥ ስንኖር እንታያለን። መንፈስ ቅዱስ ለእኔና ለእናንተ የሰጠን መንፈሳዊ ስጦታ ምን እንደሆነ ካለማወቃችን የተነሳ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማነጽ የሚረዳንን ኃይል እንደሚገባው ሳንጠቀምበት እንቀራለን። ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ለእኔና ለእናንተ ምን ዓይነት ስጦታ እንደሰጠን ማወቅ እንችል ይሆን? መንፈሳዊ ስጦታችንን ማወቅ የምንችልበት መመሪያስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይኖረን ይሆን? እግዚአብሔር እርግጥ ነው ከልጆቹ ጋር የድብብቆሽ ጨዋታ ስለማይጫወት፣ ስጦታችንን ደብቆ "ፈልጋችሁ አግኙ" በማለት ፈንታ፣ ሁላችንም መንፈሳዊ ስጦታችንን በግልጽ ለይተን

እንድናውቀው ይፈልጋል፤ የምናውቅበትንም መመሪያ ይሰጠናል። ማወቅ ብቻ ሳይሆን በተሰጠን ስጦታ እንድናገለግልበትም በር ከፍቶ ይሰጠናል።

ሰው በሕይወቱ አሸናፊ ሆኖ ለመኖር የሚያስችለውን አስፈላጊ ኃይል በውስጡ በማጣቱ ምክንያት የሚደርስበት ችግር፥ ዓለም "በኤነርጂ" (በኃይል) እጥረት ምክንያት ሊደርስበት ከሚችለው ችግር የበለጠ የከፋ ነው። ሰው በችሎታው እጅግ ልቆና ከፍ ብሎ ሊታይ ሲገባ፥ ደካማና ፍጹም ኃይል የሌለው ሆኖ ይገኛል። ኃይል ማጣቱና ደካማነቱም በልዩ ልዩ ሁኔታ ይገለጻል። የዕለት ኑሮውን ማስተካከል አቅቶት፥ ምድራዊ ሕይወቱ በዓይኑ ፊት እንዳልነበረ ሆኖ ብትንትኑ ሲወጣበት ይታያል። የሚስበው የተመረዘ ዓየር፥ የተናጋ የፖለቲካ አቋሙ አካባቢውን ለመለወጥ ኃይል የሌለው መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ምንም የሚተማመንበት የሌለው፥ ግራ የተጋባ፥ ዓላማ ቢስ እንደሆነ በየጊዜው እናያለን። በውስጡ ይነድ የነበረውን የመኖር ተስፋ "እፍ" ብሎ ያጠፋበት ኃይል ያለ ይመስል፥ በጨለማ ውስጥ ኃይል አጥቶ የሚኖር ይመስላል።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከፈቀደው ከፍተኛ ደረጃ መድረስ የሚያስችለውን ችሎታና ኃይል ሰጥቶ እንደፈጠረው እናውቃለን። ይህ እውነት ከሆነ፥ ሲፈጥረው በውስጡ ያስቀመጠው ስጦታው የት ደረሰ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የትም አልሄደም፤ ያለው በውስጡ ነው። በውስጡ መኖሩን የሚገነዘበው ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነትና ዕርቅ ሲኖረው ብቻ ነው። ጳውሎስ ለቆላስያስ ምዕመናን ሲጽፍላቸው፥ ቆላስያስ 2፥10 ላይ *"...ክርስቶስ ካላችሁ ሁሉ ነገር አላችሁ"* ይላቸዋል። ሁላችንም በክርስቶስ በኩል ሙሉ ነን። በዚህ ዓለም ላይ እግዚአብሔር በሕይወታችን እንድንፈጽመው ያቀደውን ዓላማ መፈጸም እንድንችል ልዩ የሆነ ችሎታና ኃይል ለያንዳንዳችን በውስጣችን አኑሮአል። *መመሪያ እንዲሆነን ቃሉን፥*



*አሸናፊ እንድንሆን ኃይሉን፥ እርሱን እንድንመስለው ባሕሪውን፥ እንዲሁም እንድናገለግለው መንፈሳዊ ስጦታዎቹን* ሁሉ ሰጥቶናል።

### 3. የኃይላችን ሁሉ ምንጭ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው

እግዚአብሔር እኔና እናንተን በኃይሉ አስታጥቆናል። በውስጣችን ያለን ኃይል ሁሉ ምንጩ ከሌላ የመጣ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው። ክርስቶስን ወደ ሕይወታችን በጋበዝነው ዕለት ኀይልን ተቀብለናል። ምንም ያህል ብልህና አዋቂዎች ብንሆን፥ ምንም ያህል ገንዘብ ወይንም ሀብት ቢኖረን፥ ምንም ያህል ዕውቀትና ችሎታ፥ እንዲሁም ዝናና ክብር ቢኖረን፥ ያለ እግዚአብሔር ኃይል ፍጹም ደካሞችና ዋጋቢሶች ነን።

ገንዘብ ከኪሳችን ሳናጣ፥ ዕውቀትና ዝና ሳያንሰን ውስጣችን ባዶነት ተሰምቶን ያውቃል? በየጊዜው የሚያጋጥመንን ፈተና ለመቋቋም፥ በርከት ያለ መንፈሳዊ ፍሬ ለማፍራት ምንም ዓይነት ኃይል እንደሌለን በውስጣችን የተሰማን ጊዜ አለ? ከሆነ ወደ ጌታ ፊታችንን እናዙር፤ የሚቆረቁረን ኃጢአት ቢኖር ከልባችን እንናዘዝ፤ ኃይሉን እንደገና በውስጣችን እንዲያድስ በእምነት እንጠይቀው። ከዚህ በፊት አይተነውና ቀምሰነው በማናውቀው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሞላናል።

እኔና እናንተ የምንኖረው ፍቅር የጎደላቸው፥ ከፉ፥ ጨካኞች፥ ትዕግሥት የሌላቸው፥ እንዲሁም ተበቃዮች በብዛት በሚታዩበት ዓለም ውስጥ ነው። ይህን በሚመስል ዓለም ውስጥ ስንኖር፥ ክርስቶስን መስለን መኖር በሥጋ አንችልም። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር መንፈስ በሚሰጠን ኃይል የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች፥ ይኸውም "ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋሃት፣ ራስን መግዛት" የመሳሰሉትን ፍሬዎች (ገላት. 5፥22-23) በሕይወታችን በማሳየት የክርስቶስን ማንነትና

ባህሪ ማንጸባረቅ እንችላለን። ለቤተሰባችን፥ አብረውን ለሚሠሩት፥ ለጎረቤቶቻችን በሕይወታችን ክርስቶስን ማሳየት እንችላለን።

እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ሁላችንንም አስታጥቆናል። እነዚህ ስጦታዎች በክርስቶስ ሕይወት በፍጹምነት ሲሠሩ ታይተዋል። እኛንም እነዚህ ስጦታዎች በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግና እንድንበስል ይረዱናል። ተመልካቾች መሆናችንን ቀርቶ የእግዚአብሔርን መንግሥት በማስፋፋት ተባባሪዎች እንድንሆን ያደርጉናል።

እግዚአብሔር እኔና እናንተን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች በረከት እንድንሆን ድንቅ፥ ውብ፥ አድርጎ እንደፈጠረን እናውቃለን። መንፈሳዊ ቁንጅናችን ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች እንዳይታይ የሆነበት ምክንያት፥ ኃጢአት ሕይወታችንን ስላቆሸሸውና ስላበላሸው ነው። ኃጢአት ለራሳችን፥ ለሌሎችና እንዲሁም ለእግዚአብሔር መንግሥት የማንጠቅም እንዳደረገን ለብዙዎቻችን የተሰወረ አይደለም። ዓለም የሚያየው ወደፊት መሆን የምንችለውን ሳይሆን፥ አሁን ያለንበትን አቋምና ይዞታ ብቻ ነው። ያም የማንረባ ቆሻሻዎች፥ ለማንም የማንጠቅም መሆናችንን ነው። እግዚአብሔር ሲያየን ግን አሁን በድካማችን ያለንበትን አቋምና መልክ እንደያዝን ብቻ ሳይሆን፥ ወደፊት መሆን የምንችለውንም ጭምር ነው። ያም ድንቅ፥ ዕፁብ፥ ለብዙዎች በረከት መሆን እንደምንችል ነው።

➡ ጴጥሮስን ሰዎች ሲመለከቱት የሚታያቸው ሌላ ነገር ሳይሆን፥ ተራ ዓሣ አጥማጅነቱን ብቻ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ያየው አሁን ያለበትን አቋም ብቻ ሳይሆን ወደፊት መሆን የሚችለውን ጭምር ነው። ያም የሰዎች አጥማጅ መሆን እንደሚችል ነው።

➡ ጳውሎስን (የቀድሞው ሳውል) ሰዎች ያዩትና የፈሩት፥



የክርስቲያን አሳዳጅ መሆኑን ተመልክተው ነው፤ ጌታ ግን ያየው የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ፥ የክርስቲያኖች ጠላት ሆኖ ሳይሆን፥ ወደፊት የክርስቶስ አምባሳደር፥ ስለ ወንጌል ብዙ መከራና ስቃይ የሚቀበል መሆኑን ጭምር ነው።

➡ እንዲሁም ዳዊትን ሰዎች ያዩት የአባቱን በጎች ሲጠብቅ፥ ተራ የበግ እረኛ መሆኑን ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ዓይን ሲታይና ሲመዘን ግን፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ እረኛ መሆን እንደሚችል ነው።

ሰዎች እኔንና እናንተንስ የሚያዩን በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? እኛስ ራሳችንን የምናየው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? እግዚአብሔርስ የሚያየን እንዴት ነው? እግዚአብሔር እኔና እናንተን የሚያየን ውጫችንን ብቻ ሳይሆን ውስጣችንንም ጭምር ነው። ሳሙኤል ለእስራኤል መሪ የሚሆነውን ከእሴይ ልጆች መካከል በቁመቱና በመልኩ የላቀውን ለመምረጥ ሲሞክር እግዚአብሔር እንዲህ አለው። *"...ፊቱን፥ የቁመቱንም ዘለግታ አትይ፤ ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት፤ ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል አለው"* (1 ሳሙ. 16፥7)።

እግዚአብሔር በእኛ መጠቀም የሚጀምረው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ካዋለ፥ በደሙ ፍጹም አድርጎ ካነጻና እርሱ በሚፈልገው ዓይነት አዲስ ጅማሬ ካስጀመረን በኋላ ነው። ከኃጢአታችን ፍጹም ሊያነጻን የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ያንንም ማድረግ የቻለው በመስቀል ላይ የውርደት ሞት ሞቶ ደሙን በማፍሰስ ነው። ካለፈው የኃጢአት ቆሻሻ ሊያነጻን፥ አዲስ ጅማሬ ሊሰጠን የሚችል እርሱ ብቻ ነው። ያልታወቅነውን እንድንታወቅ፥ የማንረባውን እንድንረባ፥ ተራ ሰዎች የነበርነውን ታዋቂና ተደናቂዎች ሊያደርገን የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

በራሱ ኃይል ራሱን ማሻሻል የሚችል ማንም የለም። እግዚአብሔር የራሱ ካደረገን፥ ሙሉ በሙሉ በመንፈሳዊ ጸጋ ካስታጠቀን በኋላ ለስሙና ለክብሩ፥ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ወይንም መታነጽ በእኛ ሕይወት መገልገል ይጀምራል።

ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ዝገት የሚታይባቸው፥ በማደግ ፈንታ የሚቀጭጩት፥ በክርስትና ሕይወታቸው ተስፋ የሚቆርጡት፥ አሸናፊ የክርስትና ሕይወት በመኖር ፈንታ ወደ ኋላ የሚንተቱት፥ በበደለኛነት ስሜት ውስጥ ሰላም አጥተው የሚኖሩት፥ በአገልግሎታቸው ደካማዎችና ፍሬ ቢሶች የሚሆኑት፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራና ስጦታውን እንደሚገባው ካለማወቃቸው፥ እንዲሁም ስጦታውን እንደሚገባው መለማመድ ካለመቻላቸው የተነሳ ነው።

ዛሬ የብዙዎቻችን ጥያቄ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእኔ ምንድነው? እንዴትና በምን እንዳገለግለው ይፈልጋል? የሚል ነው። ጳውሎስ ሮሜ 12፥3 ላይ *"...እንደ ባለ አዕምሮ እንዲያስብ..."* በማለት ይመክረናል። ይህን ሲል እያንዳንዳችን የግል ሕይወታችንን በሀቀኝነት መመርመር እንዳለብን ሲገልጽ ነው። እንደ *"ባለ አዕምሮ የምናስበው"* በሁለት ዓይነት አቅጣጫ ነው። ይኸውም፥

1ኛ. *"ማሰብ ከሚገባን በላይ አልፈን እንዳናስብ..."* ነው። "ለትዕቢት" ምንም ዓይነት ሥፍራ በሕይወታችን ልንሰጠው አይገባም። በትዕቢት ምክንያት የምናበላሸው፥ ትሁት ሆነን ከምናበላሸው ይበልጣል። የሚጎዳን ትዕቢት ብቻ ሳይሆን፥ ያለ አግባብ ከተጠቀምንበት ትህትናም ጎጂ የሚሆንበት ጊዜ አለ።

2ኛ. እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ *"የእምነትን መጠን እንዳከፋፈለን"* ማወቅ ነው። ይህም ማለት ሁሉም የተለያየ መጠን ያለው መንፈሳዊ ስጦታ እንደሚሰጠው ነው። ልዩነቱ በምንና በምን ይሆን? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት፥ የሰውን አካልና ተግባሩን በመዘርዘር ጳውሎስ ለቆሮንቶስ የጻፈውን የመጀመሪያውን መልዕክት ማንበብ ይጠቅማል።



*"በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ..."* በማለት ጳውሎስ በምሳሌ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን" አሠራር ያስረዳናል። ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አሠራር የበለጠ ለመረዳት፥ ብዙ ብልቶች ያሉት የሰው አካል እንዴት እንደሚሠራ ማየት ይጠቅመናል። ይሄ ምሳሌ ይህን ያህል የሚያደነጋግር አይደለም። ስለ ሰው አካል ለማወቅ ስንል ድብቅ የሆነውን *አናቶሚ* ወይንም ረቂቅ ስለሆነው ስለ *ጄኔቲክስ* ማወቅ ያስፈልገናል ማለት አይደለም። የሰው አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉትና እያንዳንዱ ብልት የተለያየ ተግባር እንደሚፈጽም ብቻ ማወቅ ነው። ለምሳሌ ዕቃ ቢወድቅብን በእጃችን እንጂ በጆሮአችን አናነሳም፤ ሙዚቃ ከፍተን ለማዳመጥ ብንፈልግ በጆሮአችን እንጂ በእጃችን አንሰማም። እያንዳንዱ የሰውነት ክፍላችን እንዲሠራ ከሚጠበቅበት በላይ አልፎ ሌላ ነገር አይሠራም። እጅ፥ "እጅ" የሚሠራውን፥ እግርም "እግር" የሚሠራውን ይሠራል እንጂ፥ "እጅ" የእግርን፥ "እግርም" የእጅን ሥራ አይሠራም።

ጳውሎስ ይህን ምሳሌ በመጠቀም የክርስቶስም አካል በዚህ ዓይነት እንደሚሠራ ይገልጻል። *"በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፤ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን ይላል"* (ሮሜ 12፥4-5)። ጳውሎስ ይቀጥልና *"እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን..."* ብሎ ስጦታዎችን ይዘረዝራል።

መጽሐፍ ቅዱስ *"እኛ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ውስጥ አንድ አካል ነን"* ሲል አማኞችን መጥቀሱ እንደሆነ እንረዳለን። በሌላ ስፍራ "የክርስቶስ አካል" ሲል ቤተ ክርስቲያንን ማለቱ

እንደሆነ እናያለን። "...ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። እርስ ዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላት ናት" ይላል (ኤፌ. 1፥22-23)። የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የሠራት እግዚአብሔር ሲሆን፥ በአንድ አምባ ገነን መሪ (ዲክቴተር) ሥር እንድትሆን አድርጎ አላበጃትም። ወይንም በዲሞክራሲ ወይንም በሕዝብ ድምጽ እንድትመራ አላደረገም። ቤተ ክርስቲያን "በእግዚአብሔር አገዛዝ" ሥር *(Theocracy)* የምትኖር ነች። ይህን ስንል ዲሞክራሲና የጠቅላላ ጉባኤ አስተ ያየት አያስፈልግም፤ ወይንም አይጠቅምም ማለታችን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ በፀሎትና በጾም መታገላችንን ችላ እንዳንል ለማሳሰብ ብቻ ነው።

## 4. ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ትክክለኛ መመሪያ የምናገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው

እግዚአብሔር ከሰጠን ታላላቅ ስጦታዎች መካከል አንደ ኛው፥ ቃሉ (መጽሐፍ ቅዱስ) ነው። ይህ መጽሐፍ የልዩ ልዩ ሃይማኖቶችን ታሪክና አመጣጣቸውን የሚተርክ የታሪክ መጽ ሐፍ፥ ወይንም "ይህን አድርጉ፤ ያንን አታድርጉ" የሚል የሕግ መጽሐፍ ብቻ አይደለም። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን እውነት በሕይወታችን መለማመድ ስንችል፥ እግዚአብሔርን ውጤታማና ፍሬያማ በሆነ መንገድ እንድናገለግለው ይረዳናል። ይህን መጽሐፍ የሚያነቡት ሁሉ የመጽሐፉን ሕግ እንዲታዘዙት ይፈልጋል። ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን ቃሉን በሥልጣ ንና በኃይል ይናገር ስለነበር፥ ብዙዎቹን ከመጠን በላይ ያስደ ንቃቸው ነበር። ያ የኢየሱስ ንግግር ዛሬ በመጽሐፍ መልክ ስለተሰጠን፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚያግዘንን መመሪያ ተቀብለናል። ቃሉን ያለማቋረጥ የሚያጠኑና በሕይወታቸው የሚለማመዱ ሁሉ፥ ከመንፈሳዊ የልብ ሕመም ማምለጥ ይች



ላሉ። ቃሉ ከሁሉም በላይ የክርስቶስን ሕያውነት በልባችን ያረ ጋግጥልናል፤ በተሻለ ሁኔታም እንድናገለግለው ያስታጥቀናል። *"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትም ሕርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል"* ይላል (2 ጢሞ. 3፥16-17)።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ማወቅ ለምን ይህን ያህል አስፈላጊ ሆነ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። በአሁኑ ጊዜ በብ ዛት የምናየው አማኞች የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴና ስጦታ ውን ለመረዳት መሠረት የሚያደርጉት የእግዚአብሔርን ቃል በመሆን ፈንታ በግል ልምምዳቸው ብቻ በመሆኑ፥ ከመስመር የወጡ ሁኔታዎች በብዛት ይታያሉ። ልምምዳችን በእግዚአብ ሔር ቃል ካልተደገፈ፥ ከምናለማው ይልቅ የምናጠፋውና የምናበላሸው የበለጠ እንደሚሆን ግልጽ ነው። የመንፈስ ቅዱስ መገለጦች (ምልክቶች) ምን እንደሆኑ ለማወቅ ብንፈልግ፥ ሐዋ ርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን የጻፈውን የመጀመሪያውን ደብዳቤ በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልገናል። አንዳንዶቻችን እግ ዚአብሔር የሚሰጠንን ስጦታ መጠቀም የምንሞክረው የእግዚአ ብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ ሳይሆን፥ በግል ልምምዳችን ላይ ብቻ ነው። ይህን ዓይነቱ መረዳት ብዙዎቹን ሲያስት፥ ቤተ ክርስቲያንን ሲከፋፍል፥ አንዳንድ ምዕመናንን ከቁጥጥር ውጪ ሲያወጣ እናያለን።

☆ ☆ ☆ ☆

ምዕራፍ 2

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለአማኞች ሁሉ የሚሰጥ ነው

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምንድነው? ይህ ጥያቄ በክር ስትና ሕይወታቸው አዲስ የሆኑት ብቻ የሚጠይቁት ሳይሆን፥ ብዙ ዘመን የቆዩትም እንደሚገባው አውቀው በግል ሕይወታቸው መለማመድ እንዲችሉ የሚጠይቁት ጥያቄ ሊሆን ይገባል። "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን" በትክክል ለመረዳት ሁለት የግሪክ ቃላትን ማወቅ ይጠቅማል።

## ❶ "ኒማቲኮስ"

*"ኒማቲኮስ"* የሚለው ቃል ትርጉሙ *"መንፈሳዊ"* ማለት ነው። ቃሉ የመጣው *"ኑማ"* ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትር ጉሙ *"መንፈስ"* ወይንም *"እስትንፋስ"* ማለት ነው። ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚያ ደርጉት ግንኙነት ወይንም የሚፈጽሙት አምልኮት ሁሉ *"መንፈሳዊ"* ይባላል። ይሄም በቀጥታ የሚመለከተው ውጪያዊ



ውን ሳይሆን ውስጣዊውን የሰውን ተፈጥሮ ነው። እርሱም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚፈጸም ግላዊ ግንኙነት እንዳለው ያመለክታል። ይኼ መንፈሳዊነት ውስጣዊ ነው ያል ንበት፥ ውጪያዊ በሆነ ነገር፥ ወይንም በሌላ ኃይል የሚለካ፥ ወይንም የሚመዘን፥ እንዲሁም ሰዎች የሚሰጡት ወይንም የሚከለክሉት ስጦታ እንዳልሆነ ለመግለጽ ነው። መንፈሳዊነት በሰውና በመንፈስ ቅዱስ መካከል የሚሆን ልዩ የሆነ ግንኙነትን ያመለክታል። አማኝ የተሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በተ ግባር ላይ ለማዋል፥ ሌላው ቀርቶ እስከ ሞት ድረስ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥበት ጊዜ እንዳለ እናውቃለን። አማኝ ቤተ ክር ስቲያንን እንዲያገለግልበት ከጌታ የተሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚገባው ባይጠቀምበት፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ እንደሚሆን ግልጽ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የአማኝ ሕይወትን የሚቀሰቅስ ወይንም የሚያነቃቃ ሞተር ነው። ለአገልግሎት የሚያነሳሳ ኃይል ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ አማኝ እግዚአብሔርን በሙሉ ኃይሉ እንዲያገለግለው የአማኙን ውስጣዊ ሕይወት ለአገልግሎት የሚገፋፋ ወይም የሚነካ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን፥ ቃሉ *"ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም፥ ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና"* (ፊልጵ. 2፥13) እንደሚለው፥ "ስጦታው" በሕይወታችን እንዲሠራ ማድረግ የምንችለው እኛ ሳንሆን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብ ሔር ብቻ እንደሆነ መረዳት እንችላለን። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አማኝ በተጠቀመበት መጠን እየታየ የሚሰጠው፥ ወይንም አማኝ በሚፈልግበት ወቅት ብቻ እየተቆነጠረ የሚሰጠው ስጦታ እንዳ ልሆነ ማወቅ ያስፈልገናል።

አሜሪካ ውስጥ የሚገኘው *የፉለር ሥነ መለኮት ትምሕ ርት ቤት* (ቲዮሎጂካል ሴሚናሪ) ፕሮፌሰር የሆኑት *ፒተር ዋግነር* የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ሲገልጹ፥ *"የመንፈስ ቅዱስ*

*ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፥ በክርስቶስ አካል ውስጥ ማገልገል የሚያስችል ለያንዳንዱ የክርስቶስ አካል (አባል) የሚሰጥ ስጦታ ነው"* አሉ።

## ❷ "ካሪዝማ"

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመረዳት የሚያስችለን ሁለተኛው የግሪክ ቃል *"ካሪዝማ"* የሚለው ቃል ነው። ይህ ቃል የመጣው *"ካሪስ"* ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም "ጸጋ" ወይንም እንዲሁ የሚሰጥ ስጦታ ማለት ነው። ይህም ሰው ለፍቶ ወይንም ደክሞ የሚያገኘው ወይንም "ለእኔ ይገባኛል! መብቴ ነው" ብሎ ጠይቆ የሚሰጠው አለመሆኑን ያሳያል። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፥ ቤተ ክርስቲያን የምትታነጽበትን አገልግሎት መስጠት እንዲችል እግዚአብሔር ለአማኝ ልዩ ኃይልን ወይንም ችሎታን እንዲሁ ይሰጠዋል። በጸጋ ስጦታው የታደለው አማኝ፥ ስጦታውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተግባር ላይ የሚያውልበትንም የአገልግሎት በር ይከፍትለታል። አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳለው የሚታወቀው፥ መንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ እርሱነቱን ለአገልግሎት ሲያንቀሳቅሰው ነው።

በአጠቃላይ *"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ"* ማለት እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፥ አማኝ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግልበት፥ ማንም ሰው ሊሸረው የማይችለውን ኃይል (ስጦታ) እንዲሁ በነጻ ሲሰጠው ነው። ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግልበት እግዚአብሔር ምን ዓይነት ልዩ የሆነ ችሎታ እንደሰጠው ለማወቅ የሚናፍቀው አማኝ፥ በተለይ ለአንዳንድ አገልግሎት ስሜቱ የበለጠ ከውስጡ ሲቀሰቀስ ይሰማዋል። ደስ በሚለውና ዝንባሌ ባለው አገልግሎት ውስጥ ተሰማርቶ እንዲያገለግል እግዚአብሔር ችሎታን መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ የአገልግሎትንም በር ይከፍትለታል። እግዚአብሔር ችሎታን ሰጥቶ



በር በከፈተለት አገልግሎት ውስጥ ሆኖ ሲያገለግል፥ የአገልግሎቱን ፍሬ ያበዛለታል፤ አገልግሎቱንም የሚያዩ ክርስቲያኖች እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ ያ አማኝ ለዚያ አገልግሎት ልዩ ስጦታ እንዳለው ይመሰክሩለታል፤ ወይንም ያረጋግጡለታል።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለአማኞች የሚሰጥበት ዋናው ምክንያት በክርስቶስ አካል ውስጥ ሆነን ሌሎችን ማገልገል እንድንችል ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚሰጠን ለግል ጥቅማችን እንድናውለው ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያንን እንድናገለግልበት ነው።

- ❐ *"ካሪዝማ"* የሚለው የግሪክ ቃል የሚያመለክተው፥ የስጦታው ምንጭ ወይንም ስጦታው ከየት እንደሆነ ነው። ስጦታው የእግዚአብሔር አምላክ ጸጋ እንደሆነ ያሳየናል። ጸጋ ስንል፥ የእግዚአብሔር ፍቅር ለማይገባው፥ ማለትም ለኃጢያተኛው እንዲሁ በነጻ መስጠት ማለት ነው።
- ❐ *"ካሪዝማ"* የሚለው የግሪክ ቃል፥ የሚያሳየን ስጦታው ሌሎችን የምናገለግልበት መሆኑን ነው። ለግል ጥቅማችን እንድናውለው የተሰጠን ስጦታ አድርገን በመቁጠር ልንደብቀው ወይም ልናጠራቅመው አንችልም። ስጦታው የሚሰጠን ለሌሎች በረከት እንዲሆን እንድንጠቀምበት ነው።
- ❐ *"ካሪዝማ"* የሚለው ቃል የሚያሳየን "ኃይሉን" ነው። ሰው በራሱ ኃይልና ችሎታ የሚጠቀምበት ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ የራሱን ኃይል የሚገልጥበት መሣሪያ መሆኑን ነው።

"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ" ሳይሆኑ "ናቸው" የምንላቸው ነገሮች ይኖሩ ይሆኑ? ብዙ ጊዜ አንዳንድ ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ምን እንደሆኑ ባለማወቅ ራሳቸውንም ሆነ የሚያገለግሉበትን ቤተ ክርስቲያን ችግር ውስጥ ሲጥሉ

እናያለን። ለመሆኑ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ" ስንል የተፈጥሮ ችሎታችንን ማለታችን ይሆን? ካልሆነ እነዚህ ሁለቱ የሚለያዩ በትና የሚመሳሰሉበት ነገር ይኖር ይሆን? የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና የተፈጥሮ ችሎታ ይመሳሰሉ እንጂ ፍጹም አንድ ዓይነት አይደሉም።

## 1. <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ ከተፈጥሮ ስጦታ በምን ይለያል?</u>

ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ የተለያየ የተፈጥሮ ችሎታ ተሰጥቶታል። ልክ እንደ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ የተፈጥሮ ችሎታም በዓይነት፥ በመጠን፥ በደረጃ ይለያያል። የተፈጥሮ ችሎታ አንዱን ከሌላው የተለየ የሚያደርገው ነው። እያንዳንዳችን የተለያየን እንድንሆን ከሚያደርጉን ነገሮች መካከል አንደኛው ገና ስንወለድ የተሰጠን የተለያየ የተፈጥሮ ችሎታችን ነው። እነዚህ የተፈጥሮ ችሎታዎች የተሰጡን በቀጥታ ከእግዚአብሔር ነው። ከእግዚአብሔር የተሰጡን በመሆናቸው ነው "ስጦታዎች" ልንላቸው የቻልነው። ለዚህ ነው ለምሳሌ ጥሩ መዘመር የሚችለውን ሰው፥ "የመዘመር ተሰጥኦ" አለው፤ እንዲሁም እግር ኳስ ጥሩ አድርጎ መጫወት የሚችለውን ሰው ስናይ፥ "እግር ኳስ መጫወት "ተሰጥኦ" አለው" የምንለው።

የተፈጥሮ ችሎታን ለመቀበል (ለማግኘት) ክርስቲያን መሆን ወይንም የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆንን አይጠይቅም። "እግዚአብሔር የለም" ብለው የሚክዱ (ኤቲየስቶች) እንኳን እጅግ የላቀ፥ ውብ፥ ድንቅ የሆነ የተፈጥሮ ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል። የተፈጥሮ ችሎታ ይኑራቸው እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለእነርሱ አይሰጥም። የተፈጥሮ ችሎታ ማለት ሰው ለተለየ ሥራ፥ ትምህርት፥ ልምምድ (ሥልጠና) የተለየ ዝንባሌ ወይንም ችሎታ ሲኖረው ነው። ልዩ ችሎታው



በአካል (በሥጋ) በአዕምሮና በስሜት ሊሆን ይችላል። የተፈጥሮ ችሎታ ከላይ እንደገለጽነው መንፈሳዊ መሆንን አይጠይቅም። የተፈጥሮ ችሎታ ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው ማለት አይደለም። የተፈጥሮ ችሎታ ጊዜያዊ ነው። ጊዜ፥ ዕድሜና ልምምድ ይወስነዋል። ማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ችሎታውን በሥራ ላይ ካላዋለው ጨርሶ ሊጠፋ ይችላል።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከተፈጥሮ ችሎታ ጋር ተመሳሳይነት ይኑረው እንጂ አንድ ዓይነት አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የእርሱን ሥራ መሥራት እንድንችል እግዚአብሔር የሚሰጠን ስጦታ ነው። *"...እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን፥ በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ..."* ይላል (1 ጴጥ. 4፥10)። እነዚህ ሁለት ስጦታዎች ብዙ የሚመሳሰሉበት ነገር አለ።

1ኛ) የሁለቱም ምንጫቸው እግዚአብሔር መሆኑ ነው። ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። *"አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?"* ይላል (1 ቆሮ. 4፥7)።

2ኛ) ሁለቱም ትክክል ባልሆነ ሁኔታ ለግል ጥቅም ሊውሉ ይችላሉ።

3ኛ) ሁለቱም እንደአጠቃቀማቸው ጥሩ ወይንም መጥፎ ውጤት ማምጣት ይችላሉ።

*ያም ሆነ ይህ "የተፈጥሮ ችሎታና" "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ"* የተለያዩ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ለተሞሉ ክርስቲያኖች ብቻ ነው። ሌላው የሚለያቸው ምክንያት ደግሞ፥ ስጦታው የሚሰጥበት "ወቅት"

ነው። "የተፈጥሮ ችሎታ ሰው ገና ከእናቱ ማህጸን ሲወጣ የሚሰጠው ስጦታ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ግን፥ እንደ ገና በመንፈስ ሲወለድና ክርስቶስን ወደ ሕይወቱ ሲያስገባ የሚቀበለው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *"...ነገር ግን በእናቴ ማህፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከ ርሁም..."* ይላል (ገላትያ 1፥15)። ሃዋርያው ጳውሎስ ገና ከመለወጡና ክርስቶስን እንደሚገባው ከማወቁ በፊት በተፈጥሮ የማስተማር ችሎታ እንደነበረው ግልጽ ነው። ጳውሎስ የመን ፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የተሰጡት ግን ክርስቶስን እንደሚገባ ካወቀና ከዳነ በኋላ ነበር። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ በመንፈሳዊ ሕይወት እንደገና ከተወለድን በኋላ የምንቀበለው ስጦታ ነው። ስጦታውም የሚሰጠን እንድናገለግልበት እንጂ፥ እንድንገለገልበት አይደለም። *"...እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ..."* ይላል (1ኛ ጴጥ. 4፥10)። *የተፈጥሮ ችሎታ* ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሌላው የሚለይበት፥ ማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ስጦታውን (ችሎታውን) ለማወቅና ለማሳደግ የሚተማመነው በራሱ ኃይል ሲሆን፥ አማኝ ግን መንፈሳዊ ስጦታውን ለመጠቀምም ሆነ ለማዳበር የሚተማ መነው በመንፈስ ቅዱስ መሆኑ ነው። አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን እንዲጠቀም ኃይልን የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው። ጳውሎስ *"ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ"* ሲል፥ "ሁሉን" የሚለው ቃል ይህንንም ያጠቃልላል ብለን እና ምናለን (ፊልጵስዩስ 4፥13)።

## 2. <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ይለያል</u>

የአማኝ ሁለተኛው ችግር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ከመን ፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መለየት አለመቻሉ ነው። *ዘጠኙ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች* በገላትያ 5፥22 ላይ ተዘርዝረዋል። *"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው"* ይላል። ከላይ እንደተ መለከትነው *"ፍቅርና ትዕግሥት"* የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ስለሆኑ፥ "እኔ የፍቅር ስጦታ ወይንም የትዕግሥት ስጦታ አለኝ" ማለት አንችልም። "ፍቅር" በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን የሚፈስ ይሁን እንጂ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ አይደ ለም። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በክርስትና ሕይወታችን ስናድግ፥ ስንበስል፥ ክርስቶስን ስንመስል፥ ለመንፈስ ቅዱስ ሁለንተናችንን ስንሰጥ፥ በሕይወታችን የሚታይ ነው። ሁላችንም በክርስትና ሕይወት የማደግ ኃላፊነት እንዳለብን ሁሉ፥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችም በሕይወታችን መታየት አለባቸው። ብዙዎቻችን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ለማወቅ እንደምንተጋው ያህል የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በሕይወታችን ለማየት መትጋት ያስፈልገናል። ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚገባን ስንራመድና ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ስንሰጥ፥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወታችን መታየት ይጀምራል። "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ"፥ አማኝ ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያመለክት፥ "የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ" ግን አማኝ ምን መምሰል እንዳለበት የሚያሳይ ነው።



*"የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ"* አማኝ የሚሰጠውን *"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ"* ተቀባይነትና ዘላቂነት እንዲኖረው በር ከፋች ነው። ስጦታ ያለፍሬ ግን ዋጋ የለውም። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህንን የተማሩት በከባድ መንገድ ነበር። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን ለማወቅ፥ ለማዳበር ብዙ ይደክሙ እንደ ነበር እናውቃለን። በሌላ በኩል ግን ቤተ ክርስቲያናቸው በብዙ አቅጣጫ ዝብርቅርቋ የወጣ ነበር። ችግራቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማነስ (ማጣት) ሳይሆን፥ *የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ*

በምዕመናኑ ሕይወት አለመታየቱ ነበር። ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13ን የጻፈው በዚህ ምክንያት ነው። የቆሮንቶስ ምዕመናን ትልቁ ጉድለታቸው በመካከላቸው ፍቅር መጥፋቱ ነበር። ይህን በመረዳት *"በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽው ጸናጽል ሆኜአለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ፥ ምሥጢርንም ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም"* ያላቸው (1 ቆሮ. 13፥1-3)። በቋንቋ የመናገር ስጦታ፥ የትንቢት መናገር፥ የጥበብና የዕውቀት መናገር ስጦታ ቢኖራቸው እንኳን፥ ፍቅር ከሌላቸው፥ ዋጋ እንደሌላቸው ይገልጽላቸዋል። *የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የማይታይበት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ አገልጋዩን ጥሩ የክርስቶስ አምባሳደር እንዳይሆን እንቅፋት ይሆንበታል።*

የአማኝ ሦስተኛው ችግር፥ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን" አማኝ ከሚጠበቅበት ግዴታ ወይንም ተግባር መለየት አለመቻሉ ነው። ለምሳሌ "እምነት" ወይንም ማመን ከማንኛውም አማኝ የሚጠበቅበት ግዴታው ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ለደህንነት የሚያበቃን "እምነት" ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ እንደሆነ ሃዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን በጻፈው መልዕክቱ ይናገራል። *"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም"* ይላል (ኤፌ. 2፥8-9)። በሌላ በኩል ደግሞ "እምነት" ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል አንደኛው እንደሆነ በገላትያ መጽሐፍ ምዕራፍ 5፥22 ላይ እናነባለን። በዕብራውያን መልዕክት ደግሞ *"ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማንችል"* እናነባለን (ዕብ. 11፥6)። ከእነዚህ ጥቅሶች የምንማራቸው ሁለት ነገሮች አሉ።



1ኛ) እያንዳንዱ አማኝ፥ በየቀኑ ያለ እምነት በመንፈሳዊ ሕይወቱ ወደፊት መራመድ እንደማይችል እንረዳለን።

2ኛ) "እምነት" ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ እንደሆነ እናያለን። ይህም "የእምነት ስጦታ" እግዚአብሔር ለጥቂት አማኞች ብቻ የሚሰጠው ስጦታ እንጂ ለሁሉም የሚሰጥ አይደለም። "የእምነት ስጦታ" በማንኛውም አማኝ ሕይወት ውስጥ ከምናየው "ከእምነት ፍሬ" ሁሉ በላይ ነው። የእምነት ዓይነቶችን ምዕራፍ 19 ላይ በሰፊው የገለጽነው ስለሆነ፥ ያንን ክፍል መመልከቱ ይጠቅማል።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ባይኖረን እግዚአብሔር በሚመርጠው ጊዜና ሁኔታ ውስጥ በሚፈልገው መንገድ አይጠቀምብንም ማለት አይደለም። ለምሳሌ እኔ በበኩሌ የፈውስ ስጦታ እንደሌለኝ በደንብ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ "የፈውስ ስጦታ ስለሌለኝ ለበሽተኛ እጄን ጭኜ አልጸልይም" አልልም። የፈውስ ስጦታ ባይኖረኝም በረጅሙ የክርስትና ዘመኔ ለብዙ በሽተኞች ጸልዬ ብዙዎች ከበሽታቸው እንደተፈወሱ አውቃለሁ።

አንድ አማኝ የተሰጠውን *"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ"* የሚጠቀምበት እስከ መቼ ድረስ ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እግዚአብሔር ስጦታውን የሚሰጠው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ እስከ መጨረሻ ዘመናችን ድረስ እንድንጠቀምበት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና አሠራሩን ለማስረዳት ሃዋርያው ጳውሎስ የተጠቀመው፥ *ብዙ ብልቶች ያሉትን አካል* እንደ ምሳሌ አድርጎ በመጠቀም ነው። መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ልዩ ልዩ ስጦታን በመስጠት፥ አማኞች በክርስቶስ አካል ውስጥ የተለያዩ ብልቶች ይኸውም፥ እንደ እጅ፥ ምላስ፥ ወይንም ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን ሆነው እንዲያገለግሉ ያደርጋል።

ጊዜ የምናጣበት ምንም ምክንያት የለም። ጠዋት ከእንቅልፋችን ስንነቃ እግራችን፣ "እግር" መሆኑ ቀርቶ "እጅ" ይሆናል ብለን እንደማንፈራው ሁሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችን፣ በክርስቶስ አካል ውስጥ ሆነን ተገጣጥሞ እንደሚሠራ ብልት ከሆንን "ይጠፋብን ይሆን?" ወይም ይወሰድብን ይሆን? ብለን አንፈራም።

ስጦታችንን ከእኛ ማንም እንደማይወስድብንና እንዲሁም አንድ ቀን እግዚአብሔር በሰጠን ስጦታ ምን ያህል ተጠቅመንበት እንደሆነ እንደሚጠይቀን ከተረዳን፣ በተሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚገባው ለመጠቀም እንድንችል፣ ሕይወታችንን በሥርዓት ለመምራት ዕቅድ ማውጣት እንጀምራለን። የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ማፋጠን የሚቻለው፣ *እያንዳንዱ አባል በጌታ ሥራ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን በማስተባበር፣ በማደፋፈርና እንዲሁም ዕድል በመስጠት ነው።* እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን ምን ያህል በተግባር ላይ እንዳዋለው ራሱን መጠየቅ ይገባዋል። *"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን በተግባር ላይ ማዋል"* ስንል፣ የምንጸልይበት፣ ቃሉን የምናነብበትና የምናጠናበትን ጊዜ ማለታችን አይደለም። እነዚህ ሁሉ የግል ሕይወታችንን የሚያሳድጉ ናቸው እንጂ መንፈሳዊ ስጦታችንን የምንለማመድባቸው አይደሉም። እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን ሰጥቶን ሳንጠቀምበት የምንቀርበት ጊዜ ይኖራል። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈለት በመጀመሪያው ዳብዳቤው 4፥14 ላይ *"...ከእጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፣ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል"* ሲለው፣ እንዲሁም በ2ኛ ጢሞ. 1፥6 ላይ ደግሞ *" ...እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው፣ እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ"* ይለዋል። በ2ኛ ጢሞ. 4፥5 ላይ ደግሞ *"...የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፤ አገልግሎትህን ፈጽም"* በማለት ይመክረዋል። እኛም የተሰ



ጠንን ስጦታ እንደሚገባው በመጠቀም ፈንታ ችላ የማለት ዝንባሌ ሊኖረን ይችላል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን በተግባር ላይ ማዋል በማንችልበት ወቅት፣ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በሕይወታችን እንዳይሠራ እናግዳለን።

ለመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ያለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ በውስጣችን ይኖር ይሆን? አንዳንድ አማኞች፣ መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው ስጦታዎች፣ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በማነጽና በማሳደግ ፈንታ ራሳቸውን ሲያከብሩበትና ከፍ ከፍ ሲያደርጉበት አይተናል። ከእኛም በፊት ቀድመው መጥተው ያለፉትም ክርስቲያኖች በዚህ ዓይነት ልምምድ ውስጥ እንዳለፉ ታሪካቸው ይመሰክራል። በአንዳንድ አካባቢ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማበላለጥ፣ ይኸውም አንዱን አተልቆ፣ ሌላውን አሳንሶ ማየት የተለመደ ነው። ለምሳሌ የመፈወስ ስጦታ ያለው አማኝ ሌላ ዓይነት ስጦታ ካላቸው የበለጠ ይከበራል፤ ይደነቃል። በዚህ ምክንያት አንዳንዶች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የሚናፍቁት፣ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ሳይሆን በሌሎች ፊት ለመከበር ወይንም ከፍ ብለው ለመታየት እንደሆነ ግልጽ ነው። የሚያሳዝነው ስጦታውን የሰጠውን ጌታ በማክበር ፈንታ ስጦታውን የተቀበለውን ሰው የምናከብር መሆናችን ነው። ስጦታውን የተቀበለው ሰው የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን በማነጽና በማሳደግ ፈንታ በስጦታው ራሱ የሚገለገልበት (የሚጠቀምበት) ይሆናል። ቀስ በቀስም ኩራት፣ ራስን ማተለቅና ማሳየት *(self-indulgence)* ውስጥ ይከተዋል። ስለዚህ ራስን ከማተለቅ ፈተና ውስጥ እንዳንወድቅ ሁላችንም መጠንቀቅ ያስፈልገናል። አንዳንድ አማኞች ከስጦታዎች መካከል "ይሄኛው ወይንም ያኛው" ይበልጣል ይላሉ። አንዱ ከስጦታዎች ሁሉ "ትንቢት መናገር" ይበልጣል ሲል፣ ሌላው ደግሞ የፈውስ ስጦታና ተአምር መሥራት ከሌሎቹ ሁሉ ይበልጣሉ ይላል። በመሠረቱ ከስጦታዎች ሁሉ "ይሄኛው ከሌላው ይበልጣል፤

ወይንም ያንሳል” ማለት አንችልም። እርግጥ አንዳንድ ስጦታዎች በተለይ በአንድ ሁኔታና አካባቢ፥ ለተለየ ጊዜ፥ አንድ የተለየ ሁኔታ ለመፈጸም ከሌሎች ስጦታዎች ሁሉ አስፈላጊ የሚሆኑበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ስጦታዎች ሁሉ ትንቢት የመናገር ስጦታ ያስፈለገበት ወቅት ነበር፤ ይሁን እንጂ፥ “ትንቢት መናገር” ከሌሎች ስጦታዎች ሁሉ ይበልጣል ማለት አይደለም።

### 3. ለመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንቅፋት የሚሆኑ ምክንያቶች

የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልካም ፍሬ እንዳይታይ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። እነርሱም፥

ሀ) አማኞች ያላቸውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አውቀው የሚገባውን ያህል ባለመጠቀማቸው ምክንያት የሚፈጠረው ችግር ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ከሰጠው የአዕምሮ ችሎታ ውስጥ፥ ሰው የተጠቀመበት ከመቶ ሠላሳ ያህሉን ወይንም ከዚያ ያነሰውን ብቻ እንደሆነ ሳይንቲስቶች ይናገራሉ። በመንፈሳዊ ሕይወትም አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን ባለማወቃቸው ምክንያት ሳይጠቀሙበት የቀሩት ከላይ ከገለጽነው ቁጥር እጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ የታወቀ ነው። አንዳንድ አማኞች ደግሞ ስጦታቸው ምን እንደሆነ ቢያውቁም፥ በስጦታቸው እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው ባለማወቃቸው ምክንያት ብቻ ሳይጠቀሙበት የሚቀሩ አሉ።

ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንዳይሠራ እንቅፋት የሚሆነው፥ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በማነጻጸራቸው ምክንያት የሚደርሰው ችግር ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሲያነጻጽሩ፥ ራሳቸውን የሚመለከቱት ከሚገባው



በታች ዝቅ አድርገው ወይንም አሳንሰው ነው። ብዙዎቹ በዚህ ዓይነት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ስለሚመለከቱ፡ “እኔ ለማንኛውም አገልግሎት ብቁ አይደለሁም” በማለት ከማንኛውም ዓይነት አገልግሎት ሸሽተው፥ ተመልካቾች ብቻ ይሆናሉ። ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጽና የሚገነባ ምንም ዓይነት ተሳትፎ አይኖራቸውም። ይህም የእግዚአብሔር ቃል ከሚያዘው ውጪ ነው። እነዚህ አማኞች ስለራሳቸው ያላቸው ግምት ከሚገባው በታች ዝቅ ብሎ ሊታያቸው የቻለው በምን ምክንያት ይሆን? በእርግጥ ዝቅተኞች ሆነው፥ ወይም ከሌሎች አንሰው ሳይሆን፥ የዝቅተኛነት ስሜት በውስጣቸው በጣም ስለሚጫናቸው ብቻ ነው። ይሄም ስሜት የሚመጣው ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር በማነጻጸር፥ ወይንም እነርሱ ሊሠሩት የሚችሉትንና የማይችሉትን ነገር በማመዛዘን ፈንታ፥ ራሳቸውን ከሌሎች ጋር ስለሚያወዳድሩ ነው። ራሳቸውን ከሌላው ጋር ሲያነጻጽሩ፥ ከሌላው አንሰው ራሳቸውን ስለሚያገኙት ፍጹም ደስታ የሸሻቸው ይሆናሉ። ሃዋርያው ጳውሎስ ስለነዚህ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል። *“ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንዶች ጋር ራሳችንን ልንቆጥር ወይም ራሳችንን ልናስተያይ አንደፍርምና፤ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ አያስተውሉም”* (2 ቆር. 10፥12)። ራሳችንን መመዘን የሚገባን እግዚአብሔር በሰጠን መለኪያ መሆን አለበት። *“እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ”* ይላል (ሮሜ 12፥3)። ጳውሎስ ስለተሰጠን የእምነት መጠን ከተናገረ በኋላ ስጦታችንን ምን እንደሆነ ይዘረዝራል። *“እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት*

*ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር"* ይላል (ሮሜ 12፥6-8)። እንግዲህ መለኪያችን ይሄ ነው። ስለራሳችን ትክክለኛ አስተያየት እንዲኖረን፥ እግዚአብሔር እንድንጠቀምበት የሰጠንን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚገባው ማወቅ ይጠቅመናል።

ሐ) የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልካም ፍሬ እንዳይታይ እንቅፋት ሊሆን የሚችለው ሌላው ምክንያት፥ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ስለሚወዳደሩና ስለሚፎካከሩ ነው። ሁላችንም ገና ስንወለድ ጀምሮ በውስጣችን የፉክክር መንፈስ እንዳለብን እናውቃለን። በህጻንነታችን ወላጆቻችን፥ ከወንድሞቻችንና ከእህቶቻችን የበለጠ እንዲወዱን ከፍተኛ ጥረት እናደርግ እንደነበረ እናስታውሳለን። በትምህርት፥ በስፖርት፥ እንዲሁም በሕብረተሰቡ መካከል በክብርና በደረጃ ከሌሎች ሁሉ በልጠን መታየት እንፈልጋለን። በመሥሪያ ቤታችንም በሥልጣን ብቻ ሳይሆን፥ በደሞዝም በልጠን ለመገኘት ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን። እንዲሁም በዕለታዊ ኑሮአችን፥ ባለን የቤት ዕቃ ከጎረቤቶቻችን ሁሉ ልቀንና ተሽለን ለመታየት እንፈልጋለን። ሌላው ቀርቶ "የእኔ ቤተ ክርስቲያን ከአንተ ቤተ ክርስቲያን ይበልጣል" በማለት ቤተ ክርስቲያንን ከሌላ ቤተ ክርስቲያን የምናወዳድርበት ጊዜ አለ። ይህን ዓይነቱ ውድድር የሥጋ እንጂ የመንፈስ ፍሬ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

እኔና እናንተ በዚህ አቅጣጫ ራሳችንን ስንመረምር፥ በውስጣችን የምናየው ለመሆኑ ምን ዓይነት ፍሬ ይሆን? ዘማሪዎች የሆንን፥ የቅርብ ጓደኛችን ከእኛ በተሻለ ድምፅ ጥሩ አድርጎ የሚዘምር መሆኑን ስንረዳ የሚሰማን ስሜት ምን ዓይነት



ነው? እግዚአብሔርን ለወንድማችን ስለ ሰጠው ስጦታ እናመሰግናለን ወይንስ ቅር ይለናል? የቅርብ ጓደኛችን በትምህርቱ ልቆ ልዩ ሽልማት ሲሰጠው ብናይ ስሜታችን ምን ይሆን? ስለ እርሱ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን? ወይንስ በቅናት ውስጣችን ይቃጠላል? በሕይወታቸው ሁሉ ነገር የተሳካላቸውን ሰዎች ስናይ፥ "አይዞአችሁ በርቱ! በያዛችሁት መንገድ ቀጥሉ!" በማለት እናበረታታቸዋለን? ወይንስ በእነርሱ ላይ ምክንያት እየፈለግን እንነቅፋቸዋለን? ለነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ በግላችን ያለንበትን ሁኔታና አቋም ያሳያል። እንግዲህ ስጦታችንን አለማወቅ፥ ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማነጻጸርና እንዲሁም ከሌሎች ጋር ውድድር መግጠም የክርስትና ሕይወታችንን ከማቀጨጩም ሌላ፥ የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደሚገባው እንዳይሠራ እንቅፋት ይሆናል። እኔና እናንተ የእግዚአብሔር ቃል፥ የእግዚአብሔር ኃይል፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር ባህሪና ስጦታው ስለ አለን፥ ችግራችን ምንም ያህል ትልቅ ቢሆን ማሸነፍ እንችላለን።

ኢየሱስ *"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው"* በማለት ትእዛዝ ሰጥቶናል (የማቴ. 28፥19)። ይህ ትዕዛዝ አንዳንዶች "የወንጌላዊነት ስጦታ" ላላቸው ብቻ የተሰጠ ይመስላቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ ትዕዛዝ እያንዳንዱን አማኝ ይመለከታል። ከዚህ ኃላፊነት ማምለጥ የሚችል ማንም የለም። ስለሆነም ይህንን ትዕዛዝ ከግቡ ለማድረስ እያንዳንዱ አማኝ ስጦታውን ማወቅ፥ መጠቀምና ማዳበር ያስፈልገዋል።

ቤተ ክርስቲያን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምዕመኗን በሚገባ ባለማስተማሯ የሚያጋጥማት ችግር ምንና ምን ይሆን?

- መከፋፈልና መለያየት በቀላሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መፈጠር ይጀምራል። ምዕመናን መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም የተለያየ ስጦታ የሚሰጥ መሆኑን ካላወቁ፥ እርስ በርሳቸው

መወዳደርና መፎካከር ይጀምራሉ።

- የመዘመር ችሎታ አለኝ የምትለዋ አማኝ፥ የመዘምራን ጓድ መሪ ለብቻዋ እንድትዘምር እየደጋገመ ዕድል ካልሰጣት ልቧ በእርሱ ላይ ቅያሜ መያዝ ይጀምራል። እርሷ መዘመር እየፈለገች የመዘምራን ጓድ ኃላፊው ተደጋጋሚ ዕድል የማይሰጣት፥ ይህቺ እህት የመዘመር ስጦታ እንደሌላት ስለሚያውቅ ሊሆን ይችላል። ያለ ስጦታዋ ብታገለግል፥ ከምታለማው ይልቅ የምታበላሸው እንደሚበልጥ የታወቀ ነው።
- ቤተ ክርስቲያን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ካላወቀች፥ መዳን በሚያስፈልጋቸው ነፍሳት ላይ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ፥ "በፕሮግራም" ላይ ብቻ ማተኮር ትጀምራለች። "እንደ ቤተ ክርስቲያን የሚጎድለን ምንድነው? ጉድለታችንንስ ለማሟላት የሚያስችለን የጸጋ ስጦታ ያለው በመካከላችን ማን አለ?" ብሎ በመጠየቅ ፈንታ፥ የምዕመናኑን ስሜት ሊቀሰቅስ የሚችል ምን ዓይነት ፕሮግራም ብናዘጋጅ ይሻላል? ብለን መጠየቅ እንጀምራለን። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት በማዘጋጀት ፈንታ፥ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ብቻ ጥረት የምናደርግ ሆነን እንገኛለን። ጥሩ ፕሮግራም ማቀናጀት መጥፎ ነው ማለታችን አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ጥሩ ፕሮግራም ማዘጋጀት እንዳለባት እናውቃለን። ይሁን እንጂ፥ የምታዘጋጀው ፕሮግራም ምዕመናኑን በመንፈሳዊ ሕይወት የሚያሳድግ፥ እንዲሁም ለአገልግሎት የሚያዘጋጅ መሆን አለበት። የምታወጣው ፕሮግራም፥ ምዕመናኑ ባለው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል።

☆ ☆ ☆ ☆



ምዕራፍ 3

# መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ሥራ

በማንኛውም አገር የሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሆኑ ተራ ምዕመናን፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ህልውናና በአማኞች ሕይወት ውስጥ ስለሚሠራው ሥራ ለማወቅ ጥማት አላቸው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምን እንደሆነ፥ በመንፈስ ቅዱስ እንዴት መሞላት እንደሚችሉ እውነቱን ለማወቅ ጥያቄ ይጠይቃሉ። አማኞች በክርስትና ሕይወታችንም ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎታችን ድካም ጎልቶ የሚታይብን፥ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን እንዴት እንደሚሠራ ካለማወቃችን የተነሳ እንደሆነ ግልጽ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ በተለይ በአሁኑ ዘመን ጎልተው የሚታዩት ስህተቶች፥ በክርስቲያኖች መካከል የሚፈጠረው መለያየት፥ አንደኛው መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት አሳብ ላይ ነው።

## ❶ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የማያጠራጥር እውነት ይዟል

ትክክለኛውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንድንረዳ፥ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፈቃድና ዓላማ ምን እንደሆነ ለይተን ማወቅ እንድንችል፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መመሪያ አድርጎ ሰጥቶናል። መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት መጽሐፍ እንጂ፥ የሃይማኖት ሥርዓትና ልምምድ፥ ወይንም ጥንታዊ የሆነ የሥነ ምግባር መግለጫ መጽሐፍ ብቻ አይደለም። ከእግዚአብሔር የተሰጠን እንጂ፥ የሰው አዕምሮ የወለደው የታሪክ ወይንም የፍልስፍና መጽሐፍ አይደለም። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት በመሆኑ፥ ይህ መጽሐፍ መተኪያ የለውም። ማንኛውም አማኝ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን እውነት በሕይወቱ መለማመድ ሲጀምር፥ እግዚአብሔርን የማገልገል ፍላጎቱና ችሎታው እየጨመረ ይሄዳል። ይህን ቅዱስ መጽሐፍ ሳይሰለች በትጋት የሚያጠና አማኝ ከማንኛውም "መንፈሳዊ ስህተት" ራሱን ከመጠበቁም በላይ፥ የክርስቶስን ሕያውነት በሕይወቱ የበለጠ እየተረዳው ይመጣል። ይህንን መጽሐፍ እንደሚገባው ሲያውቅ፥ እግዚአብሔርን ለማገልገል ከምንጊዜውም የበለጠ የተዘጋጀ ይሆናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ዓላማ ሲጽፍ፥ *"የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል"* ይላል (2 ጢሞ. 3፥16-17)። እግዚአብሔር ራሱን ስለማይቃረን፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ ምንም ዓይነት ትምህርትም ሆነ ልምምድ፥ መቀበል የለብንም። ልምምዳችን ትክክል መሆኑ ወይንም አለመሆኑ በእግዚአብሔር ቃል ይፈተናል እንጂ፥ የእግዚአብሔር ቃል በእኛ ልምምድ አይፈተንም።



## ❷ አማኝን አሸናፊ ሕይወት መኖር የሚያስችለው መንፈስ ቅዱስ ነው

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እንድንችል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል። ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን ወደ ሕይወታችን ባስገባነው ቀንና ሰዓት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን ሊሰጠን ወደ ውስጣችን እንደገባ እናውቃለን። ይሁን እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አያስፈልገንም ማለት አይደለም። ምንም ያህል የበሰለ አዕምሮ ቢኖረን፥ የረጅም ጊዜ የሃይማኖት ልምምድ ቢኖረን፥ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ፍጹም ደካሞች ነን። ለመሆኑ በየጊዜው የሚያጋጥመንን ፈተና መቋቋም አቅቶን በሕይወታችን ተደጋጋሚ የሆነ ሽንፈት ደርሶብን ይሆን? እግዚአብሔርን የሚያስከብር የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወታችን ማፍራት አቅቶን ይሆን? ለነዚህ ጥያቄዎች መልሳችን "አዎን" ከሆነ፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያስፈልገናልና እግዚአብሔር በሰማያዊው ኃይል እንዲሞላን ልባችንን እንክፈትለት። እንዲሁም ይሄ ኃይል ወደ ውስጣችን እንዳይገባ ያገደው ኃጢአት ቢኖር፥ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአታችንን እንናዘዝ፤ በኃይሉም እንዲሞላን በእምነት እንጠይቀው።

## ❸ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔር ባህሪ በሕይወታችን አይታይም

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ባህሪ መካፈል እንድንችል ከማድረጉ የተነሳ፥ እንደፈቃዱ መኖር እንድንችል ይረዳናል። በጥላቻ፥ በጭንቀት፥ በክፋትና በበቀል በተሞላ ዓለም ውስጥ፥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፥ ይኸውም *"ፍቅር፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ የዋሃትና ራስን መግዛት"* (ገላት. 5፥22) በሰው ሕይወት ውስጥ ሊኖር ይችላል ብሎ መገመት ያስቸግራል። ይሁን እንጂ፥ በብዙዎች ሕይወት

ውስጥ ከላይ ያየናቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ተገልጸው አይተናል። በዚህም እግዚአብሔር እርሱን የምንመስልበትን ልዩ ኃይልና ችሎት እንደሰጠን እናውቃለን። ስለሆነም በምንሰብከው ስብከት ብቻ ሳይሆን፥ በምንኖረውም ያማረ ሕይወት ክርስቶስን ማስተዋወቅ እንችላለን። ያለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግን የእግዚአብሔር ባሕሪ በሕይወታችን እንዲታይ ማድረግ አንችልም።

## ❹ <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሰው ጥረት የሚገኝ አይደለም</u>

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሰው ለፍቶ የሚያገኘው፥ ወይንም ስለ ቅድስናው የሚሸለመው ሽልማት ሳይሆን፥ ክርስቶስ በትንሣኤው ወቅት ለአማኞች ያስገኘው፥ እንዲሁ በነጻ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው። ስጦታውም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለአማኝ ሁሉ የሚሰጥ ነው። ጳውሎስ *"ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን። ስለዚህ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ፤ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ"* (ኤፌ. 4፥7-8) ይላል። ይሄም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለአማኞች ሁሉ የሚሰጥ ነጻ ስጦታ መሆኑን ያረጋግጥልናል። በመንፈስ ቅዱስ የተቀባውን ቃሉን፥ ኃይሉንና እርሱን የምንመስልበትን ልዩ ችሎታን የሰጠን ጌታ፥ በአካሉ ውስጥ ሆነን ቤተ ክርስቲያኑ የምትታነጽበት ምን እንደሆነ ማወቅና አገልግሎት መስጠት እንድንችል፥ የተለያየ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታንም ሰጥቶናል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በክርስቶስ በኩል የምናገኘው ወይንም የሚሰጠን ስጦታ እንጂ፥ በራሳችን ጥረትና ኃይል የምናገኘው አይደለም። እነዚህ ስጦታዎች የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እንድናገለግል የሚረዱን ብቻ ሳይሆኑ፥ በክርስትና ሕይወታችንም እንደሚገባው እንድንበስልና እንድናድግ የሚረዱን ናቸው።



እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን እንደሰጠን ስንረዳ፥ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተመልካቾች ብቻ ሳንሆን፥ የአገልግሎት ተሳታፊዎች እንድንሆን የጠራን መሆኑን እንገነዘባለን።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ "የጸጋ" ስጦታ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሀሳብ ለሮሜ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ፥ *"...እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን..."* ይላል (ሮሜ 12፥6)። *"እንደተሰጠን ጸጋ"* ሲል፥ የሁላችንም ጸጋ የተለያየ እንደሆነ ሲገልጽ ነው። ስጦታውን የሚቀበለው ሰው ተገቢም ባይሆን፥ እንዲያው በነጻ ከእግዚአብሔር የሚሰጠው ስጦታ አለው። እርሱም በሰው ፍላጎት የሚገኝ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ለፈለገው የሚያከፋፍለው ስጦታ ነው። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ማንም ስጦታውን ማግኘት አይችልም። አማኝ፥ የተሰጠውን ስጦታ "ያንስብኛል" ወይንም "እኔ የምፈልገው ስጦታ ይሄ አይደለም" ብሎ የተሰጠውን ስጦታ ችላ ሊለው አይገባም። ጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁ የሆነው ጢሞቴዎስ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን እንደሚገባው እንዳልተጠቀመበት ሲረዳ እንዲህ ሲል መከረው *"...በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል"* ይለዋል (1 ጢሞ. 4፥14)።

## ❺ <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለአማኝ በነጻ የሚሰጥ ነው</u>

*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥* መንፈስ ቅዱስ ደስ እንዳለው ለአማኞች ሁሉ በነጻ የሚሰጠው ስጦታ ነው። አማኝ ለፍቶ የሚያገኘው ወይንም ስለ መልካም ሥራው ከጌታ የሚሸለመው ሽልማት አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አማኝ ለፍቶ የማያገኘው ከሆነ፥ ስላለው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሊጨበጨብለት፥

ክበሮ ሊመታለትና የምስጋና ዘፈንም ሆነ መዝሙር ሊዘመርለት አይገባም። ይህንን ባለመረዳት አንዳንድ ክርስቲያኖች ጎልቶ የሚታይ “የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ” ላላቸው አማኞች ሲያጨበጭቡና፥ ከበሮ ሲመቱ ይታያሉ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ አማኝ ክርስቶስን ብዙ በማገልገሉ፥ ብዙ በመጸለዩ፥ ወይንም እግዚአብሔርን አባብሎ የሚያገኘው በረከት አይደለም። አማኝ በብልጥነቱ የሚያገኘው ቢሆን ኖሮ፥ ብዙ አፈ ጮሌዎች፥ ራሳቸውን “የቤተ ክርስቲያን ምሰሶ” አድርገው የሚቆጥሩት አማኞች ብቻ ስጦታ በስጦታ ይሆኑ ነበር። ስጦታውን የምናገኘው እኛ እየመረጥን ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ በፈቀደውና በመረጠው ሁኔታ ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *“ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል”* ይላል (1 ቆሮ. 12፥11)። የስጦታው አከፋፋይ ሰው ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ከጳውሎስ አጻጻፍ መረዳት እንችላለን።

## ❻ <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ማንም ማከፋፈልና መሻር አይችልም</u>

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለማከፋፈልም ሆነ ለመሻር ችሎታ ያለው ሰው የለም። አከፋፋዩ ሰው ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። አንዳንድ የዘመኑ ሰባኪዎች፥ ተፈላጊነታቸውንና ተወዳጅነታቸውን ከፍ ለማድረግ ሲሉ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለአንዳንድ ሰዎች ለማከፋፈል ሙከራ ሲያደርጉ ይታያሉ። በዚህ ምክንያት አንዳንዶች ስጦታ ሳይኖራቸው “ስጦታዬ በፓስተር እከሌ ተረጋግጦልኛል” በማለት የሌላቸውን ስጦታ፥ “አለን” በማለት ቤተ ክርስቲያንን ሲያምሱ ማየት የተለመደ ሆኗል።



## ❼ <u>ፍቅር የማይታይበት አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቢኖረውም ፍሬቢስ ነው</u>

ፍቅር የማይታይበት አገልጋይ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቢኖረውም፥ በአገልግሎቱ ተቀባይነት ያሳጣዋል (1 ቆሮ. 13፥ 1-3)። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስጦታው ሳያንሳት ፍቅር የጎደላት በመሆኗ የደረሰባትን ችግር እናውቃለን። አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳለው የምናውቀው፥ በሕይወቱ በምናየው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንደሆነ ግልጽ ነው። ከፍሬዎቹ መካከል አንደኛው “ፍቅር” ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ *“በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸው ጸናጽል ሆኜአለሁ”* ያለው (1 ቆሮ. 13፥1)። ዛሬ ብዙ አማኞች ከፍሬው ይልቅ ስጦታውን ይመኛሉ። ከሰጪው ይልቅ “ስጦታውን” ይናፍቃሉ። በዚህ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዘመናችን ብዙ ችግሮች ሲፈጠሩ እናያለን።

## ❽ <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አማኝ ራሱን እንዲያሳይበት የሚሰጠው አይደለም</u>

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ አማኝ ራሱን እንዲያሳይበት፥ ወይንም ከሌሎች አማኞች ሁሉ በልጦ እንዲታይበት የሚሰጠው ስጦታ አይደለም። ከራሱ ያልመነጨ፥ እንዲሁ በጸጋ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስጦታ ስለሆነ፥ ራሱን አተልቆ ሊያሳይ አይገባም። ዛሬ ብዙዎቻችን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የምንናፍቀው፥ የቤተ ክርስቲያን መታነጽና ማደግ አሳስቦን፥ የግንባታው ተሳታፊዎች ለመሆን ናፍቀንና ጓጉተን ሳይሆን፥ ራሳችንን የምናሳይበት፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን የምናገኝበትና ጎልተን እንድንታይ የሚያስችለን ብቻ በመሆኑ ነው። በቤተ

ክርስቲያን ውስጥ ራስን ማስቀደም፥ ራስን ማሳየት ትክክል እንዳልሆን ጳውሎስ በጻፋቸው መልዕክቶች ውስጥ እናነባለን። ይሄ ችግር ለነበረባቸው የሮሜ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ሲጽፍ፥ *"እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ"* ይላል (ሮሜ 12፥3)።

## ⑨ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያንጻል እንጂ፥ አያፈርስም

*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ዓላማውን ሲስት፥ ማለትም* አማኞች ያለአግባብ ሲጠቀሙበት፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግሮች ይፈጠራሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ *"መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል"* ይላል (1 ቆሮ. 12፥7)። *"ለጥቅም ይሰጠዋል"* ሲል፥ ስጦታው የተሰጠው አማኝ ስጦታውን ለራሱ ጥቅም ያውለዋል ማለት አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ጥቅሙ ለግለሰቡ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ነው። ጳውሎስ የትንቢት ስጦታ ያለው አማኝ ለምን እንደሚተነብይ ሲገልጽ፥ *"...ትንቢትን የሚናገር ማኅበሩን ያንጻል..."* ይላል (1 ቆሮ. 14፥4)። *"ማኅበሩን ያንጻል"* ይላል እንጂ ትንቢት ተናጋሪው *"ራሱን ያንጻል"* አይልም። በሚያስተላልፈው የትንቢት ቃል ማኅበሩን ያንጽበታል እንጂ፥ ትንቢት ተናጋሪው ልዩ ሽልማት አይሸለምበትም። ያገለግልበታል እንጂ፥ አይገለገልበትም። ሌሎችን ይጠቅማል እንጂ፥ ራሱን አይጠቅምበትም።

*"ያንጻል"* የሚለው የግሪክ ቃል የሚያመለክተው ማንባታን ነው። ትንቢትን የሚናገር ሰው ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት እንጂ ለማፍረስ፥ ቤተ ክርስቲያንን ለማጠንከር እንጂ፥ ለማዳከም አይተነብይም። ዛሬ በዘመናችን አንዳንድ "የትንቢት ስጦታ አለን" የሚሉ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን በማነጽ ወይንም በመገንባት ፈንታ ሲያፈርሱ፥ አንድ በማድረግ ፈንታ ሲከፋፍሉ፥ ምዕመናንን ወደ እግዚአብሔር በማስጠጋት ፈንታ፥ ምዕመናንን ከእግዚአብሔር ሲያርቁ፥ ቤተሰብን በመገንባት ፈንታ ትዳርን ሲያፈርሱ እናያለን። ይህን ዓይነት ውጤት ያላቸው ትንቢቶች ምንጫቸው ከማን ወይንም ከየት እንደሆን እኔና እናንተ መለየት አያቅተንም። ከእግዚአብሔር ሳይሆን፥ ከሰይጣን ወይንም ከሥጋ የመጣ መሆን አለበት። ብዙ ጊዜ በተለይ ለጆሮ ጎልተው የሚሰሙ፥ ለዓይን ደምቀው የሚታዩ ስጦታዎችን አንዳንድ ክርስቲያኖች ያለአግባብ በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንን አንድ በማድረግ ፈንታ ሲከፋፍሉበት ይታያሉ። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረው ችግር፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ያለአግባብ ከመጠቀም የመጣ ነው። እነዚህ ጎልተው የሚታዩት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያላቸው አንዳንድ አማኞች፥ "በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከሁሉም እንበልጣለን" በማለት፥ ስጦታው የሌላቸውን ክርስቲያኖች ዝቅ አድርገው ይመለከቱ ነበር። "በቋንቋ ከማይናገሩት፥ የመገለጥ ስጦታ ከሌላቸው፥ ትንቢት ከማይናገሩት፥ ሌላ ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ካላቸው አማኞች እኛ እንበልጣለን" ይሉ ነበር። ጳውሎስ ይህንን ዓይነቱን ሥጋዊነት እንዳልወደደላቸው በጻፈላቸው ደብዳቤ ውስጥ መረዳት እንችላለን።



## ⑩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አንድ ያደርጋል እንጂ፥ አይከፋፍልም

ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲናገር፥ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ አካል አድርጎ በማሳየት፥ ማኅበሩን

ባት እንጂ ለማፍረስ፥ ቤተ ክርስቲያንን ለማጠንከር እንጂ፥ ለማዳከም አይተነብይም። ዛሬ በዘመናችን አንዳንድ "የትንቢት ስጦታ አለን" የሚሉ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን በማነጽ ወይንም በመገንባት ፈንታ ሲያፈርሱ፥ አንድ በማድረግ ፈንታ ሲከፋፍሉ፥ ምዕመናንን ወደ እግዚአብሔር በማስጠጋት ፈንታ፥ ምዕመናንን ከእግዚአብሔር ሲያርቁ፥ ቤተሰብን በመገንባት ፈንታ ትዳርን ሲያፈርሱ እናያለን። ይህን ዓይነት ውጤት ያላቸው ትንቢቶች ምንጫቸው ከማን ወይንም ከየት እንደ ሆነ እኔና እናንተ መለየት አያቅተንም። ከእግዚአብሔር ሳይ ሆን፥ ከሰይጣን ወይንም ከሥጋ የመጣ መሆን አለበት። ብዙ ጊዜ በተለይ ለጆሮ ጎልተው የሚሰሙ፥ ለዓይን ደምቀው የሚታዩ ስጦታዎችን አንዳንድ ክርስቲያኖች ያለአግባብ በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንን አንድ በማድረግ ፈንታ ሲከፋፍሉበት ይታያሉ። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረው ችግር፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ያለአግባብ ከመጠቀም የመጣ ነው። እነዚህ ጎልተው የሚታዩት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያላቸው አንዳንድ አማኞች፥ "በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከሁሉም እንበልጣለን" በማለት፥ ስጦታው የሌላቸውን ክርስቲያኖች ዝቅ አድርገው ይመለከቱ ነበር። "በቋንቋ ከማይናገሩት፥ የመገለጥ ስጦታ ከሌላቸው፥ ትንቢት ከማይናገሩት፥ ሌላ ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ካላቸው አማኞች እኛ እንበልጣለን" ይሉ ነበር። ጳውሎስ ይህንን ዓይነቱን ሥጋዊነት እንዳልወደደላቸው በጻፈላቸው ደብዳቤ ውስጥ መረዳት እንችላለን።

## ⑩ <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አንድ ያደርጋል እንጂ፥ አይከፋፍልም</u>

ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲናገር፥ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ አካል አድርጎ በማሳየት፥ ማኅበሩን



የሚያያይዝና የሚያሳድግ እንጂ የግለሰቡን ጥቅም፥ ዝናና ክብር የሚያዳብር እንዳልሆነ ይገልጻል። *"በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ እንዲሁም ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፤ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን.."* ይላል (ሮሜ 12፥4-5)። በዚህ ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምዕመናኑን እርስ በርስ የሚያቀራርብና የሚያያይዝ እንጂ፥ የሚለያይ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ስጦታው ቤተ ክርስቲያንን ካላነጸ፥ ካላሳደገ፥ የምእመናኑን አንድነት ካላጠነከረ፥ የስጦታው ትክክለኛነትና እውነተኛነት ያጠራጥራል። የሚያሳዝነው በዘመናችን መከፋፈልና መለያየት በሰፊው የሚታየው "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አለን፥ በመካከላችን ይሠራል" በምንለው ክርስቲያኖች መካከል መሆኑ ነው። በልዩ ልዩ ልሳን ብንናገር፥ አስደናቂ የሆኑ ትንቢቶችን ብንተነብይ፥ እውቀትና ጥበብ ቢኖረን፥ በሽተኞችን ብንፈውስ፥ ያለንበትን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በማነጽ ፈንታ ካፈረሰ፥ የምዕመናኑን አንድነት በመጠበቅ ፈንታ ከለያየ፥ "አለን" የምንለው ስጦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ምንጩ፥ ወይንም አጠቃቀሙ ሊመረመር ይገባል።

## ⑪ <u>የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ (ማኒፌስቴሽን) ምንድነው?</u>

የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ (*manifestation*) ስንል ምን ማለታችን ነው? *ውጫዊ የሆነ፥ ስሜታችንን የምንገልጽባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች* የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ይሆኑ? ስሜታችንን የምንገልጽባቸውን ነገሮች የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ብሎ መቀበል አደገኛ ነው። "የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ምን እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆርንቶስ 12፥7-10 ላይ ይዘረዝራል። *"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል። ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥*

ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፤ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፣ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፣ ለአንድ ተአምራትን ማድረግ፣ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፣ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፣ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፣ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል…" ይላል። በዚህ ቃል መሠረት መንቀጥቀጥ፣ መንከባለል፣ መደነስ፣ ማጨብጨብ፣ መጮህ ከላይ ካየናቸው ዝርዝሮች ውስጥ ስለሌሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ናቸው ማለት አንችልም። እነዚህ ሰው በውስጥም ሆነ በውጭ ለሚሰማው ነገር ስሜቱን የሚገልጻቸው ወይንም የሚያሳይባቸው ስሜቶች እንጂ የመንፈስ ቅዱስ መገለጦች አይደሉም። አንዳንድ አማኞች ለመንፈሳዊ ዕድገታቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው መታነጽ እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስን መገለጥ በመፈለግ ፈንታ ከላይ በገለጽናቸው ስሜቶች ብቻ ረክተው ይቀመጣሉ። ሲንቀጠቀጡ፣ ሲንከባለሉ፣ ሲስቁና ሲጮሁ ይታዩ፣ ይሁን እንጂ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከዓመት ዓመት ሲያድጉና ፍሬ ሲያፈሩ አይታዩም። ያለማደጋቸው ትልቁ ምክንያትቱ ዋናውን ነገር በመፈለግ ፈንታ በመግለጫ ስሜቱ ላይ ብቻ ስለሚረኩ ነው።

## 12. <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለግል ጥቅም የሚሰጥ ይሆን?</u>

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ እንጂ አንዳንድ አገልጋዮች ትርፍ እንዲያገኙበት፣ ቀለባቸውን እንዲሠፍሩበት፣ እንዲፈሩበት፣ እንዲከበሩበትና ሌሎችን እንዲያስፈራሩበት የሚሰጥ ስጦታ አይደለም። በአሁኑ ዘመን በጣም የሚያሳዝነው፣ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚነግዱ፣ የግል ጥቅማቸውን ለማዳበር የሚሞክሩ አገልጋዮች ቁጥራቸው ብዙ መሆኑ



ነው። "የመገለጥ ስጦታ፣ የፈውስ ስጦታ አለን" በማለት በየሰው ቤት እየዞሩ የሚያስተምሩ፣ ከመስመር መውጣት አለመውጣታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊመረምሯቸው የሚችሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በማይገኙበት ስፍራ እየተገኙ የፈለጉትን የሚናገሩ፣ አዳዲስ ክርስቲያኖችን የሚያወናብዱ፣ የብዙዎቹን ትዳር የሚያፈርሱ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያምሱና የሚከፋፍሉ ወገኖች ቁጥር ጥቂት አይደለም።

ዘመናችን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሁሉም አዋቂ (ኤክስፐርት) የሆነበት ዘመን ነው። ማንም ከሌላው መስማት፣ ከማንም መማር አይፈልግም። "ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰው አያስተምረኝም፤ የምመራው ባለኝ ልምምድ ብቻ ነው" ብለው የደመደሙ ብዙ ናቸው። እንደ እግዚአብሔር ቃል "ልክ አይደላችሁም፤ ከመስመር ወጥታችኋል፤ የምትፈጽሙትን ልምምድ መጽሐፍ ቅዱስ አይደግፈውም፤ ወይንም የምትለማመዱት ልምምድ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈም" ሲባሉ፣ "እናንተ የጥንቶቹ የምተሠሩት በአሮጌ መንፈስ ነው፤ እኛ በአሁኑ ጊዜ የምንለማመደውን እናንተ ገና አልደረሳችሁበትም፤ ጌታ ለእኛ ለአዳዲሶቹ አዳዲስ ራዕይና መገለጥ እየሰጠን ነው፤ እናንተ የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴ ማመንና መቀበል ትታችኋል። እናንተ አርፋችሁ ተቀመጡና ጌታ በእኛ ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን ዝም ብላችሁ ተመልከቱ" ይላሉ። የከፋ እንደሆነ፣ መስመር ሊያስይዟቸው፣ ሊያስተምሯቸው የሚሞክሩትን ሰዎች፣ "የመንፈስ ቅዱስ ተቀዋሚ ናቸው" በማለት ራሳቸውን መከላከል ይጀምራሉ።

እዚህ ላይ አንድ እውነት እንድናውቅ ያስፈልጋል። ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የተሰጠው፣ ለግለሰብ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መሆኑ ነው። ራሳቸውን ለቤተ ክርስቲያን ማስገዛት ያቃታቸው፣ በየቤቱ እየዞሩ በቤተ ክርስቲያን

ላይ ያከረፉትን አንዳንድ ሰዎች እየፈለጉ እንዲያገለግሉበት የተሰጠ ስጦታ አይደለም። ይሄ ቢሆን እግዚአብሔር ራሱ ስለ አንድነት የሰጠውን ትእዛዝ ይቃረናል ማለት እንችል ነበር። ሃዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12፥ 13ና 14 ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ከፍተኛ ትምህርትን ሰጥቷል። ምዕራፍ 12 ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና በአንድ አካል የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንዳሉ ሲናገር፥ ምዕራፍ 13 ላይ ስለ እውነተኛ ፍቅር ይዘረዝራልI ስጦታ ያለፍቅር ዋጋ እንደሌለው ያስተምራል። ምዕራፍ 14 ላይ ደግሞ እንደገና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችንና ጥቅማቸውን ይዘረዝራል። በዚህ ሁሉ ውስጥ የምናየው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በተናጠል፥ እንዲሁም ፍቅር በሌለበት አካባቢና ሕይወት ውስጥ ሊሠራ ይችል ይሆናልI ግን የሚያስከትለው ጉዳት አለ።

☆ ☆ ☆ ☆



ምዕራፍ

4

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን እንዴት ማወቅና መቀበል እንችላለን?

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምንድነው? ይህ ጥያቄ ማንኛውም ምዕመንም ሆነ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጠይቀው ሊረዱት የሚገባ ሀሳብ ነው። መሪዎች ለራሳቸውም ሆነ ለሚመሯቸው ምዕመናን፥ መንፈስ ቅዱስ ምን ዓይነት *"መንፈሳዊ ስጦታ"* እንደሰጣቸው ለይተው ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም የምዕመናኑን ስጦታ ካላወቁ፥ እንደ ስጦታቸው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንዲያገለግሉ ዕድል መስጠት አይችሉም።

የተሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ባያውቀውም፥ ማንኛውም የዳነና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ፥ ቢያንስ አንድ ስጦታ ይኖረዋል። *"መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለያንዳንዱ ለጥቅም*

*ይሰጠዋል"* ይላል (1 ቆሮ. 12፥7)። *"ለያንዳንዱ"* ሲል፥ ለሁሉም ማለቱ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት ስጦታ የሌለው እውነተኛ አማኝ እንደሌለ ሁሉ፥ ሁሉንም ዓይነት ስጦታ የተሰጠው አማኝም የለም። ለያንዳንዱ አማኝ የሚሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ ለራሱ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ጥቅም እየታየ ስለሆነ፥ "ለእኔ የተሰጠኝ ስጦታ ከሌሎች አማኞች ሁሉ ይበልጣል" ብሎ ማወዳደርና ማበላለጥ እንደሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ስጦታቸውን በማዳነቅ ራሳቸውን በሰው ፊት አተልቀው ለማሳየት ለሚሞክሩ አማኞች ጳውሎስ ምክር ሲሰጥ፦ *"አንተ እንድትበልጥ ማን አደርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?"* (1 ቆሮ. 4፥7)) ይላል። አንድ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲሰጠው፥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት አይደለም። ቁም ነገሩ ያለው ስጦታውን በማግኘቱ ላይ ሳይሆን፥ ስጦታውን በመጠቀሙ ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከስጦታዎች መካከል አንዱ ላይ የበለጠ ትኩረት መስጠት፥ ወይንም ሌሎችን ስጦታዎች ሁሉ ችላ ብሎ በአንዱ ብቻ መገልገል፥ ቤተ ክርስቲያን በሁሉም አቅጣጫ እንዳታድግ መከልከል ይሆናል። ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንዱን ስጦታ ብቻ አተልቆ ማሳየት፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከትና ችግርን መጋበዝ ይሆናል።

## ① <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መቀበል የምንችለው እንዴት ነው</u>?

እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለጥቂቶች ብቻ የሚሰጡ አለመሆናቸውን ከተረዳን፥ እኔና እናንተ ስጦታውን መሻት የለብንም ወይ? ስጦታውንስ የምናገኘው እንዴት ነው? ይሄ ብዙዎቻችን የምንጠይቀው ጥያቄ እንደሆነ አምናለሁ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለማግኘት፥



### 1.1. በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እንደገና መወለድ አለብን

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመቀበል መጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እንደገና መወለድ አለብን። ይህ ስጦታ ክርስቶስን ለማያውቅ ለማንኛውም ሰው የሚሰጥ አይደለም። ይህንን ስጦታ ለመቀበል ኃጢአታችንን መናዘዝ፥ በክርስቶስ ማመን፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለብን።

### 1.2. ስጦታው ዛሬም እንደሚሠራ ማመን አለብን

ስጦታውን ለመቀበል፥ መጀመሪያ ስጦታው በዘመናችን መኖሩን፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚሰራ ማመን አለብን። "የለም" ብለን የምንለውን ስጦታ ለማግኘት እንደማንጓጓ የታወቀ ነው። የተለያዩ "ቤተ እምነቶች" *(denominations)*፥ ውስጥ ያሉ አማኞች ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ የራሳቸው የሆነ የተለያየ እምነትና አቋም እንዳላቸው እናውቃለን። ጎልተው የሚታዩት ሦስት ዓይነት አስተያየት ያላቸው ክፍሎች ናቸው። እነርሱም፥

1ኛ) *"ሊብራልስ"* (ላላ ያለ መንፈሳዊ አቋም ያላቸው) የሚሰጡት አስተያየት ነው። ይኸውም "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን አልነበረምI አሁንም የለም" የሚል አቋም የያዙ ናቸው።

2) "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ነበርI በእኛ ዘመን ግን የለምI አይሠራም" የሚል እምነት ያላቸው ናቸው።

3ኛ) "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ነበርI በእኛም ዘመን አለI በእኛም ዘመን ይሠራል" ብለው የሚያምኑ ናቸው።

ብዙዎቻችን በሐዋርያት ዘመን የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በእኛም ዘመን ይሠራል ብለን እናምናለን። “*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ነበር፣ አሁን ቀርቷል፣ በእኛ ጊዜ አይሠራም*” የሚሉት ለመሆኑ ምክንያታቸው ምን ይሆን? ይህን ዓይነት አቋም የወሰዱበት የተለያየ ምክንያት እንዳላቸው እናውቃለን። በተለይ አሜሪካ ውስጥ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም ብዙ እውነት የማይመስሉ፥ አጠራጣሪ ትዕይንቶች በቴሌቪዥን ይታያሉ። አንዳንድ “ስጦታው አለን” ብለው በሚሉ ሰባኪዎች አማካኝነት በቴሌቪዥን የሚቀርቡት ፕሮግራሞች፥ እንኳን የማያምኑትን፥ የሚያምኑትንም እንዲጠራጠሩ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች ሁሉ እንዳይቀበሉ፥ የበለጠ እንዲጠሉና እንዲሸሹ ያደርጋል። መጠራጠር ብቻ ሳይሆን፥ “የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እግዚአብሔር በሰጠኝ አዕምሮ እንዳል ጠቀም የሚያደርገኝ፥ እንደ አውሬ የሚያስጮኸኝ፥ እንደ እብድ መሬት ለመሬት እያንከባለለ የሚያስቀኝ፥ አጋንንት እንደያዘው ሰው የሚያንቀጠቅጠኝና መሬት ላይ ጥሎ የሚያንፈራግጠኝ ከሆነ፥ ስጦታውን አልፈልግም” እንዲሉ ያደርጋቸዋል። እነዚህ ትዕይንቶች ብዙዎቹን ወደ ጌታ በማስጠጋት ፈንታ የበለጠ እንዲሸሹ ያደርጋቸዋል።

አንዳንድ ለስሜታቸው ከፍተኛ ሥፍራ የሚሰጡ፥ ለክርስቶስ ክብር በመስጠት ፈንታ ለራሳቸው ዝናና መታወቅን የሚፈልጉ፥ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ለራሳቸው መጠቀሚያ ለማድረግ የሚሞክሩ ሰባኪዎች በሚያሳዩት ትዕይንት በመንገፍገፍ ብቻ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መናቅ፥ “*በእኛ ዘመን አይሠራም*” ብሎ መደምደም፥ ትክክል አይደለም። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አስፈላጊ ባይሆኑ ኖሮ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልተጠቀሱም ነበር።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አሁንም ይሠራሉ ብለን እናምናለን። ቤተ ክርስቲያን ልታድግ፥ ልትታነጽ የምትችለው



እነዚህን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በትክክሉና በአግባቡ መጠቀም የቻለች እንደሆነ ብቻ ነው። “የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በእኛ ዘመን አይሠራም” ብለው የሚሉ አማኞች የሚጠቅሱት ጥቅስ “*ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፣ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ*” የሚለውን ጥቅስ ነው (1 ቆሮ. 13፥8)። ለመሆኑ ይሄ ጥቅስ ምን ማለት ነው? የታሪክ ዘመን መጨረሻ ሲመጣ፥ ይኸውም፥ ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፥ ይኸውም በቋንቋ መናገር፥ ዕውቀትና ትንቢት እንዲሁም ሌሎች ስጦታዎች ያኔ አያስፈልጉምና ይቆማሉ። እነዚህ ስጦታዎች ዋና ዓላማቸው፥ እግዚአብሔርን የበለጠ እንድናውቀው የሚረዱን እንደሆኑ እናውቃለን። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ከቀድሞ ይልቅ የበለጠ እግዚአብሔርን እንድናውቀው ይረዱናል እንጂ፥ ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም እንድናውቀው ሊያደርጉን ይችላሉ ማለት አይደልም። በመጨረሻው ቀን፥ ጌታ እንደገና ሲመጣ፥ ያኔ ሙሉ በሙሉ ስለምናውቀው፥ እነዚህ ስጦታዎች አያስፈልጉንም። ለዚህ ነው ጳውሎስ “*ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፣ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ*” ያለው። የመጨረሻው ዘመን እስኪደርስ ድረስ ግን፥ እግዚአብሔርን የበለጠ እንድናውቀው የሚያደርጉን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያስፈልጉናል። በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች “ለሐዋርያት ዘመን ብቻ የተሰጠ ነው” የሚል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ሥፍራ አናነብም። ስለዚህ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመቀበል፥ ስጦታው ዛሬም ለእኛ የተሰጠ መሆኑን፥ በእኛም ዘመን እንደሚሠራ ማመን አለብን።

## 1.3. እግዚአብሔር ስጦታዎችን ለአማኞች እንደሚሰጠን ማመን አለብን

ስጦታው መኖሩን ብቻ ሳይሆን፥ በዘመናችን ለአማኞች የሚሰጥ መሆኑን ማመን አለብን። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን መፈለግ ያለብን በእምነት ነው። እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ

ስጦታዎችን ለሁላችንም እንደሚሰጠን ካላመንን፥ ስጦታውን መፈለግ አንችልም። ለብዙዎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምኞት ብቻ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለላቁት፥ ለጥቂቶች ብቻ የሚሰጥ ሽልማት የሚመስላቸው አሉ። በዚህ ምክንያት ለመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ራሳቸውን ብቁ አድርገው አያዩም፤ እግዚአብሔርም ብቁ ስላልሆኑ ስጦታ የሚሰጣቸው መስሎ አይሰማቸውም። ይሁን እንጂ በተቻላቸው መጠን እርሱን በቅንነት ለማገልገል የሚሞክሩ አማኞች አሉ።

እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን አንድ ነገር ቢኖር፥ እግዚአብሔር ማንንም በስጦታው ሳያስታጥቅ "አገልግሉኝ" ብሎ የማይልክ መሆኑን ነው። ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው። *"እኔ መረጥሁአችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ ሄዳችሁ ብዙ ፍሬ እንድታፈሩ፥ ፍሬአችሁም ነዋሪ እንዲሆን ሾምሁአችሁ"* (የዮሐ. 15፥16)። እዚህ ላይ እኔና እናንተ የምንጠይቀው ጥያቄ፥ "ሰው ብዙ ፍሬ ማፍራት የሚችለው እንዴት ነው?" የሚል ነው። ከባድ ኃላፊነት አይደለም? እርግጥ ከባድ ነው። ይሁን እንጂ የሚቻልበትን መንገድ ተናግሯል። *"በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ፤ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ላይ ካልኖረ በቀር በራሱ ብቻ ማፍራት እንደማይቻለው እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ማፍራት አትችሉም"* ይላል (የዮሐ. 15፥4)። በዚህ ቃል መሠረት ፍሬ ማፍራት የምንችለው የኃይል ሁሉ ምንጭ በሆነው አምላክ ውስጥ የኖርን እንደሆን ብቻ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን ማገልገል የምንችለው፥ እርሱ ራሱ ባስታጠቀን ወይንም በሰጠን መንፈሳዊ ስጦታ በመጠቀም ብቻ መሆን አለበት። ጴጥሮስ *"የተለያዩትን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታዎች በታማኝነት በማስተዳደር ከእናንተ እያንዳንዱ በተሰጠው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል"* ይላል (1 ጴጥ. 4፥10)። በዚህ ቃል መሠ



ረት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለያንዳንዳችን ተሰጥቶናል፥ ካልሆነ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እየዋሸ ነው ማለት ነው። ከሁለት አንዱን ማመን አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ አይዋሽም ካልን፥ ስጦታውን በእምነት መቀበል ሊኖርብን ነው። ለሁላችንም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚሰጠን ካመንን፥ ስጦታውን እንዲሰጠን በእምነት መጠየቅ አለብን።

## 1.4. ስጦታውን በግላችን መፈለግ አለብን

ሐዋርያው ጳውሎስ *"...የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ይልቁንም ትንቢት የመናገር ስጦታን በብርቱ ፈልጉ..."* ይለናል (1 ቆሮ. 14፥1)። ጳውሎስ *"በተለይ ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ"* ሲል፥ ከስጦታዎች ሁሉ *"ትንቢት መናገር"* ይበልጣል ማለቱ አይደለም። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በተለይ በዚያን ጊዜ ከስጦታዎቹ ሁሉ አስፈላጊው ወይንም የበለጠ የሚጠቅማቸው "ትንቢት መናገር" ስለነበረ ብቻ ነው። ዛሬ እኛ ባለንበት ዘመን፥ በተለይ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ትንቢት የሚናገሩ ነብያት ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ ጥቃቅኑን ችግር መፍታት አቅቷቸው ሲጎነጣጠሉ፥ ሲበታተኑ እናያለን። እንደነዚህ ዓይነቶቹ የበለጠ መሻት የሚያስፈልጋቸው ከትንቢት ስጦታ ይልቅ *"የጥበብና የዕውቀት መናገር"* ስጦታ ነው። ያም ሆነ ይህ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በመካከላችን እንዲሠሩ ከፈለግን፥ እግዚአብሔርን በእምነት መጠየቅ አለብን።

## ② <u>አማኝ ስጦታውን ማወቁ ምን ይጠቅመዋል?</u>

አማኝ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማወቁ ለመሆኑ ምን ይጠቅመዋል? አማኝ ስጦታውን ባያውቀውም፥ እግዚአብሔር ለጥቂቶች ብቻ ሳይሆን ለያንዳንዱ አማኝ የተለያየ

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እንደሚሰጥ አይተናል። አማኝ ከእግዚአብሔር የተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳለው መረዳት ሲችል፥

## 2.1. እግዚአብሔር በሕይወቱ ልዩ ዓላማ እንዳለው ይረዳል

እግዚአብሔር ለያንዳንዱ ልጆቹ ልዩ የሆነ ዓላማ እንዳለው ሲረዳ፥ አማኝ የተበታተነና ዓላማ ቢስ የነበረውን ሕይወቱን በእግዚአብሔር ዓላማ ሥር ያሳርፋል። ልቡ በእግዚአብሔር ላይ እንዲታመን ይሆናል። "እኔንም ቢሆን እግዚአብሔር ይጠቀምብኛል" በማለት ልዩ ደስታ ይሰማዋል። ቀደም ሲል ስለ ራሱ ይሰማው የነበረውን የዝቅተኛነት መንፈስ ያጠፋለታል። አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳለውና እንዲሁም በተሰጠው ስጦታ የእግዚአብሔርን አካል (ቤተ ክርስቲያንን) ለማነጽ እየተጠቀመበት መሆኑን ሲያውቅ፥ ደስ ይለዋል። እንዲሁም እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሥፍራ ለማገልገል ምንም ዓይነት ከፍተኛ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ይሆናል።

## 2.2. የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቁን ይረዳል

አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን ማወቅ ያለበት ሌላው ምክንያት፥ ስጦታውን እንዲያውቅ በእግዚአብሔር ቃል ስለ ታዘዘ ነው። ጳውሎስ *"ወንድሞቼ ሆይ! አሁን ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እውነተኛውን ነገር እንድታውቁ እፈልጋለሁ"* ይላል (1 ቆሮ. 12፥1)። አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደተሰጠውና ስጦታው ምን እንደሆነ ካወቀ፥ በስጦታው መጠቀም እንዳለበት ማወቁ ብቻ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥርም መሆኑን ይረዳል። *"በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል"* ይላል (1 ጢሞ. 4፥14)።



## 2.3. ፍሬያማ አገልግሎት መስጠት መቻሉን ያያል

አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን ሲያውቅ፥ በክርስቶስ አካል ውስጥ ፍሬያማ በሆነ መንገድ እንዲያገለግል ያስችለዋል። *"ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ፥ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን፥ በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል..."* ይላል (1 ጴጥ. 4፥10-11)። አማኝ በተሰጠው ጸጋ መሠረት ማገልገል እንዲችል፥ መጀመሪያ የጸጋ ስጦታው ምን እንደሆነ ማወቅ አለበት። ይህ የጸጋ ስጦታ የተሰጠው፥ ለግለሰብ መጠቀሚያ ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽበት የተሰጠ ስጦታ እንደሆነ በተደጋጋሚ ገልጸናል። "የመገለጥ ስጦታ፥ ትንቢት የመናገር ስጦታ፥ የፈውስ ስጦታ መንፈስ ቅዱስ ለእኔ እንደሰጠኝ የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ስለማያምኑና ስላልተቀበሉኝ፥ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አልፈልግም፤ የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል መሆን አልፈልግም። ጌታ የጸጋ ስጦታን አትረፍርፎ ስለሰጠኝ፥ ከፈለጋችሁ እቤቴ ድረስ እየመጣችሁ፥ ወይንም እቤታችሁ እየመጣሁ ላገልግላችሁ" የሚሉ ክርስቲያኖች ቢኖሩ፥ ትልቅ የመንፈሳዊ ችግር እንዳለባቸው በግልጽ እናያለን። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የሚሰጥ ስጦታ እንጂ፥ ያኮረፉ ክርስቲያኖች ቤታቸው ተቀምጠው የሚጠቀሙበት መሣሪያ አይደለም።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሰፊው የሚናገረው ክፍል 1ኛ ቆሮ. ምዕራፍ 12 ነው። ይሄ ምዕራፍ በሦስት ክፍል ተከፍሎ እናያለን።

አንደኛው፥ ከቁጥር 1 እስከ 12 ያለው ሲሆን፥ ይሄ ክፍል የሚናገረው ስለ ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ነው።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከቁጥር 12 እስከ ቁጥር 26 ሲሆን፥ ይሄ ክፍል የሚናገረው በአንድ አካል የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንዳሉ ነው።

ሦስተኛው ክፍል፥ ከቁጥር 27 እስከ 31 ሲሆን፥ ይሄ ክፍል የሚናገረው፥ እንደ ገና ስለ ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ነው። ይሄም በግልጽ የሚያሳየን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በተናጠል ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "በሕብረት" እንደሚሠራ ነው።

እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች "በሕብረት" ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ጳውሎስ በተለያየ ሁኔታ ሲገልጸው እና ያለን። *"ዐይን እጅን አንተ አታስፈልገኝም! ሊለው አይችልም፤ ራስም እግርን አንተ አታስፈልገኝም ሊለው አይችልም..."* ይላል (12፥21)። ዝቅ ይልና *"...በአካል ክፍሎች መካከል መለያየት ሳይኖር እርስ በርሳቸው እንዲተሳሰቡ ነው፤ አንዱ የአካል ክፍል ሲሠቃይ፥ ሌሎችም የአካል ክፍሎች በሙሉ አብረው ይሠቃያሉ፤ አንዱ የአካል ክፍል ሲከበር ሌሎቹም የአካል ክፍሎች አብረው ከእርሱ ጋር ይደሰታሉ"* ይላል (12፥25-26)።

## ③ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን እንዴት ማወቅ ይችላል?

ብዙዎቻችን "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዬን እንዴት ማወቅ እችላለሁ? እግዚአብሔር ምን ዓይነት ስጦታዎችን እንደ ሰጠኝ እንዴት ለይቼ ማወቅ እችላለሁ? ስጦታዬን ለማወቅ የምከተለው

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም 70

አንደኛው፥ ከቁጥር 1 እስከ 12 ያለው ሲሆን፥ ይሄ ክፍል የሚናገረው ስለ ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ነው።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከቁጥር 12 እስከ ቁጥር 26 ሲሆን፥ ይሄ ክፍል የሚናገረው በአንድ አካል የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንዳሉ ነው።

ሦስተኛው ክፍል፥ ከቁጥር 27 እስከ 31 ሲሆን፥ ይሄ ክፍል የሚናገረው፥ እንደ ገና ስለ ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ነው። ይሄም በግልጽ የሚያሳየን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በተናጠል ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "በሕብረት" እንደሚሠራ ነው።

እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች "በሕብረት" ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ጳውሎስ በተለያየ ሁኔታ ሲገልጸው እና ያለን። "ዐይን እጅን አንተ አታስፈልገኝም! ሊለው አይችልም፤ ራስም እግርን አንተ አታስፈልገኝም ሊለው አይችልም..." ይላል (12፥21)። ዝቅ ይልና "...በአካል ክፍሎች መካከል መለያየት ሳይኖር እርስ በርሳቸው እንዲተሳሰቡ ነው፤ አንዱ የአካል ክፍል ሲሠቃይ፥ ሌሎችም የአካል ክፍሎች በሙሉ አብረው ይሠቃያሉ፤ አንዱ የአካል ክፍል ሲከበር ሌሎቹም የአካል ክፍሎች አብረው ከእርሱ ጋር ይደሰታሉ" ይላል (12፥25-26)።

③ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን እንዴት ማወቅ ይችላል?

ብዙዎቻችን "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዬን እንዴት ማወቅ እችላለሁ? እግዚአብሔር ምን ዓይነት ስጦታዎችን እንደ ሰጠኝ እንዴት ለይቼ ማወቅ እችላለሁ? ስጦታዬን ለማወቅ የምከተለው

ቅደም ተከተል የያዘ መመሪያ አለ ወይ?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። አንድ ነገር እርግጠኞች እንሁን። ያም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ምንጊዜም ቢሆን የድብብቆሽ ጨዋታ የማይጫወት መሆኑን ነው። ስጦታችንን ደብቆ "ፈልጋችሁ አግኙት" አይለንም። ስጦታችንን እርሱ እንደሚያየው እኛም በግልጽ እንድናየው ይፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ የሰጠንን "የጸጋ ስጦታ" ለይተን ለማወቅ ምን ማድረግ አለብን?

### 3.1. *መጸለይ*

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ለማወቅ መውሰድ ያለብን እርምጃ፥ አንደኛው መጸለይ ነው። እግዚአብሔር የማናውቀውን እንድናውቅ የምንችልበትን መንገድ ከፍቶልናል። ያም ጸሎት ነው። ያዕቆብ *"...ስለማትጸልዩ የምትፈልጉትን ነገር አታገኙም"* ይለናል (ያዕ. 4፥2)። እግዚአብሔር ስጦታችንን እንዲያሳየን ጸልየን፥ ስጦታችንን ማውቅ ካልቻልን፥ ያዕቆብ በ4፥3 ላይ *"ብትጸልዩም የጸሎታችሁን መልስ የማታገኙት የለመናችሁትን ነገር በሥጋዊ ደስታ ላይ ለማዋል በክፉ አሳብ ስለምትጸልዩ ነው"* እንዳለው፥ እኛም ምናልባት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ለማወቅ የፈለግነው ለሥጋዊ ፍላጎታችን ማርኪያ እንዲሆንልን በመፈለጋችን ይሆናል። በአካባቢያችን የምናውቃቸው አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምክንያት ያገኙትን ዝናና ክብር ስንመለከት፥ እኛም እንደነርሱ ለመሆን በመመኘት "ጌታ ሆይ! ለእኔስ የሰጠኸኝ ስጦታ ምንድነው?" ብለን እንጠይቅ ይሆናል። በሐዋርያት ዘመን *"ሐዋርያት እጆቻቸውን ሲጭኑባቸው መንፈስ ቅዱስ ለሰዎቹ መሰጠቱን ሲሞን ባየ ጊዜ ገንዘብ አመጣላቸውና እኔም እጄን የምጭንበት ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ። ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፥ የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ*



*ለማግኘት በመፈለግህ ገንዘብህ ካንተ ጋር ይጥፋ! ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ስላልሆነ አንተ ከዚህ ነገር ክፍል ወይም ዕጣ የለህም"* እንዳለው እናስታውሳለን (የሐዋ. 8፥ 18-21)። በአሁንም ዘመን እንደ ሲሞን "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን" ለራሳቸው ክብር ሲሉ የሚመኙ አሉ።

ምን ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደተሰጠን ማወቅ የምንፈልገው ለምን ይሆን? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራሳችንን ከፍ ከፍ ልናደርግበት፥ ወይንም ራሳችንን ልናሳይበት ይሆን? ስጦታችንን አውቀን ሌሎችን እንድናገለግልበት ከሆነ፥ "ጌታ ሆይ! ቤተ ክርስቲያንን እንደሚገባኝ ማገልገል እንድችል፥ ስጦታዬ ምን እንደሆነ አሳውቀኝ" ብለን ብንጸልይ፥ እግዚአብሔር ለጥያቄያችን መልስ ይሰጠናል። መንፈስ ቅዱስ ዓይናችንን ከፍቶ የሰጠን ስጦታ ምን እንደሆነ ያሳየናል። ማሳየት ብቻ ሳይሆን የምናገለግልበትንም በር ይከፍትልናል።

### 3.2. የሚሰማንን ስሜት መመርመር

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን ለማወቅ ሌላው ማድረግ ያለብን ነገር ቢኖር ስሜታችንን መመርመር ነው። "አማኝ በአገልግሎቱ ደስ የሚለው ከሆነ፥ አንድ ልክ ያልሆነ ነገር በሕይወቱ መኖር አለበት" ብለው የሚያምኑና የሚያስቡ አንዳንድ አስተማሪዎች እንዳሉ እናውቃለን። ይህ ከእውነት የራቀ አስተያየት ነው። እግዚአብሔርን ማገልገል ደስታ ያለበት እንጂ የሚጨፈግግ አይደለም። ደስ ብሎን እንጂ፥ በግድ ወይንም ደስ ሳይለን እንድናገለግለው አይፈልግም። እግዚአብሔር የሥነ-ልቦና ይዞታችንን፥ የሚሰማንን ስሜት ሁሉ ያውቃል። ስንሠራው ደስ የሚለንን ሥራ ስንሠራ የበለጠ ፍሬያማ እንደምንሆን ያውቃል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚሰጠን መንፈሳዊ ስጦታ ደስ ብሎን የምንሠራው እንጂ እየጨፈገግን፥ ደስታ

ሸሽቶን የምናገለግልበት የአገልግሎት ስጦታ አይደለም።
መንፈሳዊ አገልግሎት በፈቃደኝነት ደስ ብሎን የምናገለግለው
እንጂ፥ በግድ አይደለም። በምናገለግለው አገልግሎት ደስ
ካለን "ከእግዚአብሔር ነው" ወይም ስንሠራው ደስ ካላለን
ደግሞ "ከእግዚአብሔር አይደለም" ብሎ በአጠቃላይ መገመት
ግን ስህተት ላይ ስለሚጥለን መጠንቀቅ አለብን። መስበክ ደስ
የሚላቸው ክርስቲያኖች ሁሉ ሲሰብኩ ደስ ስላላቸው ስጦታው
አላቸው ማለት አይደለም። ደስ ያላቸው ምክንያት የክርስቶስን
እውነት ለሰዎች መግለጻቸው ሳይሆን፥ በሰው ዘንድ እንዲታወቁ
ስላደረጋቸው ይሆናልና፥ የደስታቸውን እውነተኛ ምክንያት
መመርመር ይገባቸዋል።

### 3.3. የአገልግሎታችንን ፍሬ መመዘን

ስናገለግል በአገልግሎታችን ፍሬ እናያለን? የምናስተ
ምር ከሆነ ስናስተምር ሰዎች ይባረካሉ? ይማሩበታል? በወን
ጌል ስብከታችንስ ሰዎች ወደ ጌታ ይመጣሉ? ስጦታችን የበለጠ
ግልጽ እየሆነልን የሚመጣው፥ በተግባር ላይ ስናውለውና በአገ
ልግሎታችን ፍሬ የማየት ዕድል ሲኖረን ነው።

### 3.4. የሰዎችን ምስክርነት መስማት

ሌሎች ሰዎች በአገልግሎታችን እንድንቀጥል ያደፋፍ
ሩናል? ሁሉም ባይሆኑ፥ ዕድገታችንን የሚናፍቁ አንዳንድ
ሰዎችን እግዚአብሔር በዙሪያችን እንዳስቀመጠ እናውቃለን።
ክርስቲያን ጓደኞቻችን፥ መጋቢዎቻችን፥ የቤተ ክርስቲያን
ሽማግሌዎች ስለምንሰጠው አገልግሎት ምን ይላሉ? አንዳንድ
ጊዜ እኛ ራሳችንን ከምናውቀው የበለጠ ሌሎች ሰዎች ያውቁ
ናል። ያለ ቦታችን ሆነን የምናገለግል ከሆነ፥ "የምታገለግለው



ያለቦታህ ነው" ይሉናል? ወይንስ "ለዚህ አገልግሎት እግዚአብ
ሔር ስጦታውን እንደሰጠህ እናምናለን! በርታ! ቀጥል" ብለው
ስለ አገልግሎታችን መልካም ምስክርነት ይሰጣሉ?

### 3.5. መንፈስ ቅዱስ ለልባችን የሚሰጠንን ምስክርነት ማዳመጥ

መንፈስ ቅዱስ መዳናችንን ብቻ ሳይሆን ስጦታችንም ምን
እንደሆነ በልባችን ይመሰክርልናል። ክርስቲያን የፈለገውን ዓይ
ነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እየመረጠ አይቀበልም። መንፈስ
ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልገውን ስጦታ ስለሚያውቅ
የሚያከፋፍለው እርሱ ራሱ ነው። *"...መንፈስ ቅዱስ እንደ
ፍላጎቱ ለእያንዳንዱ ሰው የተለየ ስጦታ ይሰጠዋል"* ይላል (1
ቆሮ. 12፥11)። የትኛውም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቢሆን
ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ሕይወት መኖራችንን ወይንም
በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከሌሎች የተሻልን ወይንም የበለጥን
ክርስቲያኖች መሆናችንን አያሳይም።

## ④ <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታችንን በተግባር ላይ ማዋል አለብን</u>

ስጦታዎችን መጠየቅ ወይንም መፈለግ ብቻ ሳይሆን፥
ከተሰጠን በኋላ በስጦታዎቹ ማገልገል አለብን። ጳውሎስ *"የተ
ለያዩትን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታዎች በታማኝነት በማስተ
ዳደር ከእናንተ እያንዳንዱ በተሰጠው የጸጋ ስጦታ ሌላውን
ያገልግል"* ይላል (1 ጴጥ. 4፥10)። እዚህ ላይ ልብ ማለት
የሚገባን፥ "ራሱን ያገልግል" ሳይሆን "ሌላውን ያገልግል" ነው
የሚለው። ስጦታው ያላቸውን፥ በስጦታቸው እንዲጠቀሙበት
ማነሳሳት፥ ማደፋፈርም፥ አለብን። አማኝን ለአገልግሎት

የምናነሳሳበት አንደኛው መንገድ፥ የአገልግሎት በር ለያንዳንዱ አማኝ በመክፈትና በስጦታቸው መሠረት እንዲያገለግሉ ዕድል በመስጠት ነው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አገልግሎቶች ሁሉ እነርሱ ብቻ ካልሠሩት ሥራው በትክክል የሚሠራ ስለማይመስላቸው፥ ሌሎች እንዲያገለግሉ የአገልግሎት በር አይከፍቱም። ብዙ ጊዜ በክርስቲያኖች መካከል ግጭት የሚፈጠርበት አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፥ አማኞች በተሰጣቸው ስጦታ የሚያገለግሉበት ዕድል ስለሚያጡ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *"...እጆቼን በአንተ ላይ በጫንሁ ጊዜ የተሰጠህንና የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድ ታነሣሣው አሳስብሃለሁ" ሲለው እንሰማለን* (2 ጢሞ. 1፥6)።

ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ዋና ዓላማው እግዚአብሔርን የበለጠ እንድናውቀው ማድረግ ነው። ብዙ ጊዜ ግን የእግዚአብሔርን ኃያልነት በማየትና በማድነቅ ፈንታ፥ ስጦታው የተሰጠውን ሰው እናደንቃለን። ስጦታው ላይ ትኩረት በመስጠት፥ ሰጪውን እንረሳለን። ብዙዎቻችን እግዚአብሔር መልካም ስጦታ እንደሚሰጥ እናውቃለን፤ ስጦታውን እንዲሰጠን ለምን እንደምንፈልግ ግን አናውቅም። ዓይናችን የሚያርፈው በሰጪው ላይ ሳይሆን ብዙ ጊዜ በስጦታው ላይ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ስጦታውን ተቀብለው በተሰጣቸው ስጦታ ደስ ብሏቸው በማገልገል ፈንታ፥ የሚያጉረመርሙ አንዳንድ አማኞች አሉ። እንዲኖራቸው የሚፈልጉት፥ በአደባባይ ጎልተውና ደምቀው እንዲታዩ የሚያደርጋቸውን ስጦታ ብቻ ነው። እንደ ህጻን ልጅ ስጦታቸውን ከሌላው አማኝ ስጦታ ጋር በማወዳደር "እግዚአብሐር ለእኔ ትልቁን ስጦታ አልሰጠኝም" በማለት የሚያኮርፉ፥ በተሰጣቸውም ስጦታ የማያገለግሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች በየቤተ ክርስቲያኑ ይገኛሉ። በዚህ ዓይነት ሁሉም በተሰጠው የጸጋ ስጦታ ካላገለገለ፥ ቤተ ክርስቲያን ትጎዳለች።



## ⑤ ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ስንት ናቸው? አንዳንድ ክርስቲያን ጸሀፊዎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በተለያየ መደብ፥ ወይንም ክፍል ከፋፍለው ይዘረዝሯቸዋል። ይሄኛው ወይንም ያኛው አመዳደብ ልክ ነው ወይንም ልክ አይደለም ማለት የምንችልበት መመሪያ የለንም። አንዳንዶች ስጦታዎቹን በሦስት መደብ (ክፍል) ይከፍሏቸዋል። ይኸውም፥

### *(ሀ.1) በንግግር የሚገለጡ ስጦታዎች፥*

1. በጥበብ የመናገር ስጦታ
2. በእውቀት የመናገር ስጦታ
3. በልዩ ልዩ ዓይነት ልሳን የመናገርና በልሳኖች የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ
4. ትንቢት የመናገር ስጦታ
5. የወንጌል ሰበካ ስጦታ
6. የማስተማር ስጦታ
7. የመምከር ስጦታ
8. የሐዋርያነት ስጦታ
9. የእረኝነት ስጦታ

### *(ሀ.2) በአገልግሎት የሚገለጡ ስጦታዎች*

1. የማገልገል ስጦታ
2. የመለገስ ስጦታ
3. የአስተዳደር ስጦታ
4. የምሕረት ስጦታ

## (ሀ.3) በኃይልና በተአምር የሚገለጡ ስጦታዎች

1. የመፈወስ ስጦታ
2. ተአምር የመሥራት ስጦታ
3. የእምነት ስጦታ
4. መናፍስትን የመለየት ስጦታ

ጳውሎስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር፥ "የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ" ብሎ ይጀምራል። የመጀመሪያዎቹን ዘጠኝ ስጦታዎች *"የመገለጥ ስጦታዎች"* ያላቸው፥ ስጦታዎቹ በአማኞች ሕይወት ሲሠሩ የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ መገለጥን የሚያሳዩ በመሆናቸው ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፥ ከሌሎች ስጦታዎች የበለጠ ትኩረት ለመስጠት የሞከርነው *"የመገለጥ ስጦታዎች"* ላይ ነው። ይህንን ለማድረግ የመረጥንበት ዋናው ምክንያት፥ አንዳንድ ስህተቶች የሚደረጉት በነዚህ ስጦታዎች ላይ ስለሆነ፥ ስህተቶቹን ለመጠቆም እንዲያስችለን አስበን ነው።

በኤፌሶን 4፥11 የተጠቀሱት አምስቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፥ *"...ሐዋርያት... ነቢያት... የወንጌል ሰባኪዎች... እረኞች... አስተማሪዎች..."* የማዕረግ ሳይሆኑ፥ የአገልግሎት ስሞች ናቸው። አማኝ "ነብይ" የሚል ስም ስለተሰጠው ብቻ "ነብይ" አይሆንም። ነብይ መሆን የሚችለው እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ፥ እግዚአብሔር በጠራው ስፍራ ስጦታውን በተግባር ላይ ያዋለው እንደሆነ ብቻ ነው። እነዚህ አምስት ስጦታዎች ክርስቲያኖችን ለአገልግሎት የሚያስታጥቁ፥ የክርስቶስ አካል፥ ማለትም ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ የክርስቶስ ወኪል እንድትሆን የሚያበቃትን አገልግሎት እንድትሰጥ የሚረዱ ናቸው። ስጦታው ያለው ሰው፥ ራሱ እንዲገለገልበት የተሰጠው ሳይሆን የተቀሩትን የክርስቶስ ብልቶችን የሚያገለግልበት ነው።



ከላይ የተዘረዘሩት የማነቃቂያ ስጦታዎችም፥ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው። እነዚህን ስጦታዎች ለመቀበል እኔና እናንተ ተገቢዎች ባንሆንም፥ እግዚአብሔር ስለወደደን ብቻ ስጦታውን በነጻ ሰጠን። መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያነቃቁ በመሆናቸው ነው "የማነቃቂያ ስጦታዎች" ብለን የጠራናቸው። እነዚህ የተፈጥሮ ባህሪያችንን የሚቀርጹ ስጦታዎች ናቸው። እግዚአብሔር የመፍቀድና የመምረጥ መብት ሰጥቶ ስለፈጠረን በነዚህ የማነቃቂያ ስጦታዎች ልንጠቀምባቸው፥ ወይንም ላንጠቀምባቸው እንችላለን። እነዚህን ስጦታዎች በጥቅም ላይ ለማዋል፥ ስጦታዎቹ ምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚሠሩ ማወቅ ስለሚያስፈልገን፥ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እያንዳንዱን ስጦታ ለመመርመር እንሞክራለን።

☆ ☆ ☆ ☆